# ጥያቄ እና መልስ
# በዕብራውያን ክፍል II

በመጀመሪያ “ስለሚስቴ ጸልዩላት” የሚል መልእክቱን የተላከላችሁ እያንዳንዳችሁን ማመስገን እፈልጋለሁ። በጣም፡ በጣም ታምማ ነበር። ምን እንደ ሆነ አናውቅም፡ እና ምን እንደ ተደረገም አናውቅም፡ በጣም ኃይለኛ ትውከት እና አንድ መቶ አምስት ያህል ትኩሳት፡ እራሷንም እስከመሳት የሚያደርሳት ነበር፡ በበረዶ ብርድ ልብስ ተጠቅልላ ማቆየት ነበረባት። ስለዚህ... አሁን ግን ደህና ነች። ትኩሳቱ አልቋል፡ እና ደህና ነች። በጣም ተዳክማለች፡ እንደሚመስለኝም፡ አስር ፓውንድ ቀንሳለች። እስከ ዛሬ... ከእሁድ ወዲህ የመጀመሪያ ጉርሻዋ ዛሬ ማታ ቀመሰች። እናም በጠና ታምማ ነበር፡ እኛም ስለእሷ በጌታ አምነናል፡ እሱም አሻግሯታል። አሁንም ጉልበትዋ እንዲመለስ መጸለያችሁን እንድትቀጥሉ ልናሳስባችሁ እንፈልጋለን።

304 አሁንም፡ በሚቀጥሉት ቅዳሜና እሁድ፡ ጌታ ቢፈቅድ፡ ወደ ማያሚ መሄድ አለብኝ። የብዙ ዓመት ጓደኛዬ፡ ወንድም ቦስዎርዝ፡ ወደ ቤት እየሄደ ነው፡ እና አሁን መቶ አመት ሊሞላው ነው። ደውሎልኛል፡ እና “ወንድም ብራንሃም፡ ከመሄዴ በፊት አንድ ነገር ልነግርህ እፈልጋለሁ፡ ፈጥነህ ናና እየኝ፡” ብሎኛል። እና... እርሱም፡ እንደምታውቁት፡ ስለ እኔ መጸለይ፡ እና ከመሄዱ በፊት እጁን እንዲጭንብኝ የሚፈልግ ይመስለኛል።

305 እና እኔም—የዘመኖቼ መጨረሻ እንደ ኤፍ.ኤፍ. ቦስዎርዝ እንዲያልቁልኝ ተስፋ አደርጋለሁ። በአለም ላይ ከማውቃቸው ሰዎች ሁሉ፡ በአለም ላይ ካየኋቸው ሰዎች ሁሉ፡ ማለቴ፡ እንደ—አገልጋይ፡ እንደ ኤፍ.ኤፍ. ቦስዎርዝ ለመሆን በጣም የተመኘሁት ሰው፥ አጋጥሞኝ አያውቅም። በዓለም ዙሪያ፡ በየትኛውም ቦታ፡ አንድም ሰው ቢሆን፡ ስለ ኤፍ.ኤፍ. ቦስዎርዝ “ክርስቲያን” ስለመሆኑ ካልሆነ በቀር ሌላ ሲነገርበት ሰምቼ አላውቅም፡ እንዲሁም “ትክክለኛ ወንድም” ነው ይሉታል።

306 “መለያየት በጊዜ አሸዋ ላይ አሻራ ይተውልናል።” በጣም ጥሩ ወንድም ነው፡ አሁን በእውነት አርጅቷል፡ ወደ መቶ ይጠጋል። ስለዚህ በቃ ወ—ወደ ቤት መሄዱ ነው፡ አልቋል፡ እሱም ነግሮኛል። መሄዱ እንደሆነ፡ እና እየተጠባበቀ እንዳለ አውቋል። በህይወቱ ውስጥ እጅግ የተወደደው ጊዜ አሁን እየተጠባበቀ ባለበት ጊዜ ነው። ነገር ግን እንደሚሄድ እንደሚያውቅ ተናግሯል።

307 “በዚህ ሳምንት ሚቺጋን መሄድ አለብኝ፡ ወንድም ቦስዎርዝ፡” አልኩት።

308 እርሱም፡ “ይሁን፡ ቢሆንም ለረጅም ጊዜ አታድርገው፡ ወንድም ብራንሃም፡ ከእንግዲህ ብዙ ጊዜ አልቆይም። በየጊዜው እየደከመኝ ነው።”

309 ስለዚህ እጅግ ወዳጄ ከመሆኑ የተነሣ፡ ወደዚያ የማልወርድበት ምክንያት የለም። አሁን፡ በረራ ማድረግ ካለብኝ፡ ምናልባት ለእሁድ ምሽት ወደ ኋላ

በበረራ እ—እመለሳለሁ፥ ካልሆነም፡ እንግዲህ፡ መንዳት ይጠበቅብኛል፡ ምናልባትም ትንሽ ረዘም ያለ ጊዜ ሊወስድብኛ ይችላል።

310 እና ለወንድም ቦሰዎርዝ ጸልዩ። ምናልባት እግዚአብሔር... ሽማግሌውን ፓትርያርክ ሲወስደው፡ የእሳት ሠረገላ ልኮ እንዲያስነሣው ጸልዩ፡ እያችሁ። እወደዋለሁ፡ እሱ ለእኔ እንደ አባት ነበረ።

311 ሌላ ሽማግሌም አለ... እሱ እና ወንድም ሴዋርድ። እ—እኔ አረጋውያንን አከብራለሁ፡ እ—እወዳቸዋለሁ። ሽማግሌው ወንድም ሴዋርድም፡ በተመሣሣይ መልኩ፡ እንቀላፋ። እርግጥ ነው፡ ወንድም ሴዋርድ እንደ ወንድም ቦሰዎርዝ፡ ዕድሜው በጣም ያረጀ አልነበረም፡ አይመስለኝም።

312 እና ለወንድም ቦሰዎርዝ ጸልዩ። በዙርያው ያለ ነገር ሁሉ ጽጌረዳ አይደለም፡ ግን እ—እሱ... የእናንተን ጸሎት ይፈልጋል፡ ለከንቱ ነገር ሳይሆን ፍላጎቱ... እግዚአብሔር በሰላም እንዲቀበለው ነው።

313 አሁን... እና፡ ነገም፡ ጌታ ቢፈቅድ፡ ማስታወስ እንፈልጋለን፡ ከዚህ ቤተ ክርስቲያን ወዳጆችን አንዱን፡ ወንድም ሶል ኮትስን እንቀብራለን። ለብዙ ዘመን እዚህ ኖሯል፡ ለዓመታት በፖስታ ቤት ውስጥ ይሰራ ነበር። እናም በቀደምለት ምሽት በቬተራንስ ሆስፒታል አረፈ። እኔና ወንድም ኮክስ እሱን ለማየት ሄድን፡ እና... በጣም ቀንሷል። እና አሁን አንቀላፍቷል፡ ክርስቲያን ሆኗል። እና ነገ ከሰአት በኋላ፡ ወንድም ኔቪል እና እኔ ከኮትስ ቀብር አስፈጻሚ ዘንድ ቀብሩን እናስፈጽማለን። የኔቪል ትሪዮዎች ይዘምራሉ፥ እና ወንድም ኔቪል እና እኔ፡ አገልግሎቶቹን እንከፋፈላለን። ማለትም፡ በሚዳ ጉዳይ ምክንያት፡ መቼ እንደምናዘጋጀው እርግጠኛ አልነበርኩም። እና፡ ስለዚህ፡ የቀብር ስነ ስርዓቱ ነገ ከሰአት በኋላ በአንድ ሰአት ላይ፡ በኮትስ የቀብር አስፈጻሚ ዘንድ ይፈጸማል።

314 ከዚያም፡ እርብ፡ በሁለት ሰአት፡ ሚሰተር ዊለር። ፖድ ዊለር ብለን እንጠራዋለን፥ እሱ ነው፡ ነገሩ ረስቼዋለሁ... እና፡ ታውቃላችሁ፡ ጋ—ጋዜጣው ላይ አይቼ ማን እንደነበረ ረሳሁት፡ በኋላ ግን ገባኝ። ለዓመታት ጎረቤታችን ነበር፡ እና—እና እሱም አርፏል። በቀደም ምሽት፡ እዚሁ በቤተክርስቲያኑ ፊት ለፊት ነበር፡ እና ወደ ቤተክርስትያን እንዲመጣ ለማድረግ እየሞከርኩ ነበር። በቀደም ምሽት፡ ከሶስት ሳምንታት በፊት፡ እዚያው ቆሞ ነበር፡ እና ወደ ቤተክርስቲያን እንዲመጣ ለማሳመን ሞከርኩ። ምክንያቱም፡ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚሄድ ወይም ምንም ዓይነት ሙያ ያለው አይመስለኝም፡ ሆኖም የባፕቲስት ሰባኪ የሆነ ወንድ ልጅ አለው። ነገር ግን እኔ እስከማውቀው ድረስ ምንም አይነት ሙያ አልነበረውም፡ እና አሁን እግዚአብሔርን ለመገናኘት ሄዷል። ስለዚህ የእሱም እርብ ከሰአት በኋላ በኮትስ የቀብር አስፈጻሚ ሁለት ሰአት ላይ ይደረጋል። እና ደግሞ፡ ወንድም ኔቪል እና ሌሎቹ፡ እና በዚያ የቀብር ሥነ ሥርዓት ላይ ይዘምራሉ።

315 ስለዚህ፡ አንዳችሁም በአገልግሎቶቹ ላይ ለመሳተፍ የምትፈልግ ከሆነ፡ ነገ በሁለት ሰዓት ላይ፡ ወይም፡ ነገ አንድ ሰዓት ላይ ነው። ትክክል ይመስለኛል። አይደል፡ ወንድሜ? እና ሌላኛው፡ ሁለት ሰዓት። ልክ ነው? ሁለት፡ በኮትስ የቀብር ሥነ ሥርዓት አስፈጻሚ ላይ።

316 እና አሁን፡ እሁድ ጥዋት... ቅዳሜ ሰርጭቱ ይደረጋል። እና እንዴት እንደሚሆን፡ ወንድም ኔቪል፡ ምናልባት ያኔ ያሳውቃችኋል... የፈውስ አገልግሎቱ

በእሁድ ማታ ላይ እናደርግ ይሆናል፡ ወይም ወንድም ቦስዎርዝን ለማየት ወደ ፍሎሪዳ ከበረርኩ—እዚህ በምንደርሰበት በይትኛውም ሰዓት ይሁን። ከእሱ መለየት እንዴት እንደምችል አላውቅም፡ እሱ እንደዚህ አይነት ውድ ወዳጄ ነው። እና፡ ምናልባትም ጌታ ከፈቀደ፡ በዚህ ምድር ለመገናኘት፡ የመጨረሻ ጊዜያችን ይሆናል። እርሱም... ወዲያውኑ ከእሱ መለየት እችላለሁ ወይስ አልችልም እንጃ፥ እና ከእሱ መለየት አልፈልግም፡ ነገር ግን፡ እንዴት እንደሆነ ታውቃላችሁ፡ ሌሎች ማድረግ ያለብን ነገሮች አሉ።

317 አሁን እና ጓደኞቼ የሆኑ ሰዎች ብዙ ባይኖሩም፡ እዚህ አንድ ነገር መናገር የምፈልገው ነገር አለ።

318 እህት ስሚዝን እዚያ በማየቴ ደስተኛ ነኝ። ለመጀመሪያ ጊዜ ከረጅም ጊዜ በኋላ አየኋት። እህት ስሚዝ እንዴት ነሽ? ለመጨረሻ ጊዜ ያየሁሽ፡ የዛሬ አንድ አመት፡ አቤት... [እህት ስሚዝ ተናገረች—አርታዒ።] በቤንተን ሀርቦር፡ አንዴ ወደዚያ እንደምመጣ ተስፋ አደርጋለሁ። በጣም ጥሩ። ለመጨረሻ ጊዜ ያየሁሽ፡ በሉዊስቪል የቀብር ሥነ ሥርዓት ላይ ይመስለኛል። እና እህት ስሚዝን በደንብ አስታውሳለሁ። ወደ ቤተ ክርስቲያን ስንሄድ... በጭነት መኪና ይዣት እመጣ ነበር። አሮጌው የከሰል ሬንጅ በጀርባው ላይ ተንጠልጥሎ እና መከላከያዎቹ ወደ ላይ እና ወደ ታች ያፈሳሉ፡ እጅግ ይቀዘቅዝ ነበር፥ እና እኔም፡ አንዱ እግሬ ከውጭ ይሆናል። ኦህ፡ ማይ! ያን ጊዜ በወንዙ ውስጥ እጅግ ብዙ ውኃ ይጎርፋል፡ እህት ስሚዝ። አዎን፡ ወዳጆች። እንደው፡ ስለ እነዚያ ውድ ትዝታዎች ጌታን እናመሰግናለን፡ አሁንም እንወደዋለን።

319 ሌላ ነገር ደግሞ፡ ምናልባት አንድ ሰው የሚያስገርም ነገር ነው፡ በቀደም ማታ... እዚህ መንገድ ላይ ከወንድም ፍሊማን ጋር እየተነጋገርኩ ነበር። እና አንዳንድ ጊዜ ሰው እንዲህ ይላል፡ "አገልግሎቱ እንዳለቀ፡ ወንድም ብራንሃም እንዲነሳ እና እንዲሄድ የሚያደርገው ምንድን ነው? "

320 ምክንያቱ ይሄ ነው፡ ሚስቴ ብቻዋን ናት። አያችሁ? እና ንግግር ከጀመርኩ፡ እስከ እኩለ ሌሊት ድረስ መናገር እችላለሁ፡ እሷም በዚያ ውስጥ፡ አብዛኛው ጊዜ ብቻዋን ትቀመጣለች። እና ወደ እሷ ለመመለስ፡ የምፈጥንበት ምክንያት ይህ ነው፡ አያችሁ፡ ማታ ሲሆን፥ ንግግር ከጀመርኩ፡ ብዙ እናገራለሁ። **ከአንዱ** ጋር ግማሽ ሰዓት ያህል እናገራለሁ። እንዲሁ በቀላሉ ሄጄም፡ "ዛሬ ማታ እንዴት **ነህ**? አንተስ እንዴት **ነህ**? አንተ እንዴት **ነህ**? " እልልም እንዲህ አላደርግም። ንግግር እጀምራለሁ፥ ሌላኛውም ስለ አንድ ነገር ይናገራል፡ ከዚያ አንድ ሰዓት እቆያለሁ። አያችሁ? እና ለዚህ ነው፡ እሷም አዘጋጅታ ትጠብቃለች እና ወዘተ። እና ለዚህ ነው። ጓደኞቼን ማግኘት እና እጃቸውን መጨባበጥ እና አብሮነታችንን መግለጽ ወዘተ ካለመፈለግ ነው፡ ብላችሁ እንድታስቡት አልፈልግም፡ ነገር ግን እንደዚያ አይነት ጉዳዮች ስለሚገጥሙን ነው።

321 እንግዲያውስ፡ አሁን፡ ሁሉም ለታመሙና ለተቸገሩት ይጸልይ።

322 ወይዘሮ ሃርቪም በዚያ ሁሉ ችግር ውስጥ ነች፡ ቢሆንም እየተሻላት ነው። አዎን ወዳጄ። ሌላው አንድ ነገር... እ... እኔ እስከሚገባኝ ድረስ፡ ምናልባት፡ የሆነ ሰው፡ ወይም ዶክተር እዚህ ሊኖር ይችላል። እና በዚህ መድረክ ላይ ከተሳሳትኩ፡ እግዚአብሔር ይቅር በለኝ። ነገር ግን በሴቲቱ ላይ ላደረጉት ነገር እግዚአብሔር ዶክተሮችን እንደሚጠይቃቸው አምናለሁ። በ—በቀዶ

ጥገና አምናለሁ፡ በመድሃኒት አምናለሁ። በትክክል፡ አምናለሁ። ለመኪናዎች እና ለመሳሰሉት መካኒኮችን እንደላከ ሁሉ፡ እግዚአብሔር እኛን እንዲረዱን ወደዚህ የላካቸው ይመስለኛል። ነገር ግን ያቺን ምስኪን ሴት፡ ሐኪሙ አስተኝቷታል፡ እና እንዲህ አለ፡ "በካንሰር ተጠቅታለች፡ ምንም ማድረግ አይቻልም።" ብዙ ልጆች ያሏት ምስኪን እመቤት።

323 ወደ እሷ ወርጄ፡ እንዴት እንደሆነ በጸሎት ልገልጽላት ሞክሬአለሁ... እ—— እና የሃያ-አምስት አመት ገደማ፡ ወጣት ሴት ነች። እግዚአብሔርም ሕፃንዋን እንዴት እንደፈወሰው፡ "ተአምረኛው ህፃን" ይባላል በልጆች ሆስፒታል ውስጥ፡ የማጅራት ገትር በሽታ ታሞ ገብቶ ነበር። እና እንደዚህ ካለው አስቃቂ ሁኔታ—— ብላቴናውን፡ ጌታ ወዲያውኑ ፈወሰው። ለእነዚያም፡ ለዶክተሮቹ፡ ከአእምሮ በላይ ሆነባቸው። ወደ ወይዘሮ ሃርቪ ወረድኩ፡ እና እንዲህ አልኳት፡ "አሁንስ፡ ወይዘሮ ሃርቪ፡ ዶክተሮቹ ተሰፋ ቆርጠውብሻልን?

324 "አዎን፡ ጌታዬ። እንዲሁ ነው... "

325 ባልዋም "አዎን፡ ምንም ማድረግ አልተቻለም፡ ሙሉ በሙሉ በካንሰር ተጠቅታለች፡" አለ።

326 እኔም እንዲህ አልኳቸው፡ "እንግዲህ፡ አሁን ማድረግ ያለብን፡ እግዚአብሔርን መታመን፡ እግዚአብሔር እንደ——እንደሚፈውስሽ... ማመን ነው።" እኔም አልኳት፡ "እንዴት ይሆናል፡ ካንሰሩ ቶሎ ላይለቅ ይችላል፥ ከጸለይን ግን፡ የካንሰሩ ህይወት ይለቃል። ለጥቂት ጊዜ ታመሽ ልትቆይ ትችያለሽ፡ እ——እና" "ፈጣን እፎይታ ልታገኚም ትችያለሽ" አልኳት። "ከጥቂት ቀናት በኋላ ህመሙ ሊጸናብሽ ይችላል፡" አልኳት። ግን አልኳት፡ "እምነትሽ ካንሰሩን መጋፈጥ አለበት።" እንዲህ አልኳት፡ "ካንሰሩ ሲለቅሽ፡ ትሞቻለሽ። ማለቴ ካንሰሩ ሲሞት፡ አንቺ ትኖሪአለሽ።" እኔም አልኳት፡ "አሁን እንጸልያለን።"

327 እናም ጸለይን፡ እና ባየሁት ምስክርነት ሁሉ፡ እግዚአብሔር የሴቲቱን አካል ነካ። እና ወዲያውኑ ተሻላት፡ እናቴንም ለመጠየቅ ሄደች፡ በአካባቢው ዙሪያውን ጎበኘች፡ (እንዲህ አይነት መከራ ውስጥ በነበረችበት ጊዜ) ምንም አይነት ህመም አልነበራትም። ከዚያም ከሶስት ቀን ገደማ በኋላ እንደገና መታመም ጀመረች።

328 እና በኋላ ግን እንደተረዳነው ከተማው አንድ ነገር ማለታቸውን አወቅን "ዶክተሮቹ ቀዶ ጥገና ቢያደርጉላት፡ የዶክተሩን ሂሳብ እንደሚከፍሉ።"

329 አሁን ከተሳሳትኩ፡ እግዚአብሔር ይቅር ይበለኝ። ነገር ግን ወጣቷን እናት ወሰደው፡ "ጊኒ ፒግ" አስመሰሏት። ወደዚያም ወሰዷት፡ የሆድ እቃዋን፡ እና ሌላ ሁሉ ከሆዷ አሰወጡት። ሁለቱንም ከሸንት እና ከአንጀት ክፍሎች ወሰደው፡ በጎን በኩል ለጠጡት። እና በቀዶ ጥገናው ጠረጴዛ ላይ ለዘጠኝ ሰዓታት እና የሆነ ነገር ቆየ። ነርሷ እንዲህ አለች፡ "ውስጧን ከቦታ ቦታ ሲያመላልሷት፡ የእርድ ሰፍራ መሰለ፡ እና የፕላስቲክ ኦቫሪዎች እና የፕላስቲክ ቱቦዎችን አስቀመጡ።" ግልጽ ቢሆንም፡ ግን ያ እውነት ነው። እና የፕላስቲክ አንጀት እና የመሳሰሉት ነገሮች ከተውባት፡ ምስኪኗ እናት፡ በዛ ጥገና ላይ አስተኝተው አቆዩአት። እንደ እኔ አስተሳሰብ፡ እንዲህ እላለሁ፡ ዶክተሮቹ በግድያ ወንጀለኞች ናቸው።

330 እንዲህ አለቻቸው፡ “ወንድም ብራንሃም ጸልዮልኛል፡” ብላቻዋለች። እንዲህም አሉ፡ “እንደምናምነው ይህ ካንሰር… ካንሰሩ ሞቷል።”

331 አሏትም፡ “እኔ እነግርሻለሁ፡ ‘ካንሰርሽ በህይወት አለ።’”

332 እንዴትስ እንደዚያ ይላል? እሱ የሚገኘው ከውስጥ ነው፡ ኤክስ-ሬይ ሊያየው አይችልም። ካንሰር’ኮ… ካንሰር በኤክስ-ሬይ መለየት አይቻልም፡ እሱ ራሱ ሥጋ ነው፡ አይታይም። ማድረግ የሚችሉት አንድ ነገር ብቻ ነው፡ ሴትየዋን ቀደው መቆራረስ ብቻ ነው። ይኸው ነው። እንግዲያውስ እንዲህ ላለች ምስኪን እናት፡ እሷን የመሰለ ሰው “ጊኒ ፒግ” ከማስመሰል ይልቅ እምነቷን በእግዚ አብሔር ላይ እንድትፈትን ባደርግ እመርጣለሁ። አሁን እኔ—ከተሳሳትኩ፡ የሆነ—የተሳሳተ አመለካከት ኖሮኝ ከሆነ፡ እግዚአብሔር ይቅር እንዲለኝ እፈልጋለሁ፡ አያችሁ። ምክንያቱም በኦፕራሲዮኖች እንደማላምን ወይም በዶክተሮች እና ነገሮች እንደማላምን እንድታስቡኝ አልፈልግም። ያ ምንም ችግር የለውም። ነገር ግን አንድን ሰው ከመክፈታችሁ በፊት ምን እየሰራችሁ እንደሆነ ማወቅ ያለባችሁ ይመስለኛል፡ ለእንደዚህ አይነት ምርምር ብቻ አትጠቀሙባቸው። ትክክል ነው። እና አሁን፡ በእርግጥ፡ መኖር አትችልም። ይኼው ነው። እሷ በህይወት ከኖረች፡ በእርግጥ ከተከሰቱት ታላላቅ ተአምራቶች አንዱ ይባላል። ሴቲቱም አንጀቷ በአንድ በኩል፡ ኩላሊቶቿም በሌላ በኩል ሲሠሩ ስትመለከት፡ በቃ ዝም ብላ **እንደዚህ** አለፈች፡ አለፈች… ለምን፡ ለምንም አይጠቅምም… ምስኪኗ ሞታለችና። እና የሃያ-ሁለት ወይም ሃያ-አምስት አመት ሶስት ወይም አራት ትንንሽ ልጆችን የምታሳድግ እናት ናት። በህይወቴ ከሰማሁት በጣም አሳዛኝ ነገር። እኔም እላለሁ፡ “እንደ እኔ አስተሳሰብ፡ የዶክተሩ ጥፋት ነው… ” ከተማው ክፍያውን ስለሚፈጽም ሴቲቱን ለምርምር ብቻ ከተጠቀመባት፡ እንግዲያውስ ስህተት ነው፡ መፈቀድ የለበትም።

333 [አንድ ወንድም እግዚአብሔር ሴቲቱን ሊመልሰላት ይችል እንደሆነ ጠየቀ—አርታዒ።] እንግዲህ፡ እልሃለሁ፡ ወንድሜ፡ የማይቻል ነገር አይደለም። እና እ—እንዲህ አይደለም… የ—የሚቻል ነገር ነው፡ አንጻራዊም ነው። ምክንያቱም በካሊፎርኒያ ውስጥ ክንዱ የተቆረጠበት ሰው አውቃለሁ (እናንተ ራሳችሁ በጋዜጣ ላይ አንብባችሁታል)፡ ተጸለየለት፡ እና **ይሄኛው** ክንዱ **ከዚህ** ተቆርጦ ነበር፡ አሁን ግን እስከ ጣቶቹ ድረስ እንደገና በቅሏል፥ ከክርኑ ጀምሮ፡ በእጅ አንጓው፡ እና እጁ፡ እና የጉልበቶቹ ክፍሎች እስከ ጣቶቹ ድረስ አድጓል፡ አያችሁ። ይመስለኛል፡ **በሄራልድ ኦፍ ፌይዝ**፡ በየወሩ ታገኙታላችሁ። እጆቹን **እንደዚህ** ሲያወጣ እንኳን፡ እጁ ከተቆረጠበት፡ ያደገበት ቦታ ላይ አሳይቷል። በየወሩ እንዴት እንደሚመጣ፡ ለአንድ አመት ያህል አሳየ።

334 [ያ ወንድም እንደገና ተናገረ—አርታዒ።] በእርግጥ፡ ልክ ነው፡ አምናለሁ… እ—እ—እጅግ አንስተኛ አጋጣሚ ነው፡ አያችሁ፡ እጅግ አነስተኛ አጋጣሚ ነው። አንዳንዴ እንዲህ እሰማለሁ። አሁን፡ ስለ ወንድም ቦስዎርዝ፡ አንዴ ምሽት ላይ ለአንድ ሴት ጸለዮ ነበር። በሰብሰባዬም አንዴ አጋጥሞኛል። የወንድም ቦስዎርዝ ግን ወዲያውኑ ነበር፥ የእኔ ያ እንዲሆን ጊዜ ፈጅቷል።

335 ለአንዲት ሴት ጸለየ… አሁን፡ የሴትየዋን ምስክርነት አነብቤአለሁ። ካንሰር ታማ፡ አፍንጫም አልነበራትም፥ አፍንጫዋን በልቶት ነበርና። በሚቀጥለው ማለዳ ግን ሴትዬዋ አፍንጫዋ ተመለሰ። አሁን፡ ይህንን አውቃለሁ… አሁን፡

ያም የወንድም ቦሰዎርዝ፡ **ክራይስት ዘ ሂለር** በተባለው መጽሐፉ ውስጥ ይገኛል፡ ይመስለኛል፡ ወይም፡ እንደኛውም፡ **ዘ ጃይ ብሪንገር**። አሁን፡ በሰሟ እና በአድራሻዋ፡ በሴትየዋ የተሰጠ ምስክርነት ነው። እና ይህ ነገር መፈጸሙን የሚያረጋግጡ፡ ጎረቤቶች እና ዶክተሮች እና ሁሉም በዙርያዋ አሉ።

336 አሁን፡ በሊትል ሮክ፡ አርካንሳስ፡ ክፍል ውስጥ አንድ ምሽት፡ እዚያ ጸለይሁ... ሊትል ሮክ አይደለም፡ በጆንስቦሮ ነው። ጸለይኩኝ... እንዲህ አልኩኝ፡ "ለመጨረሻው ሰው እስክጸልይ ድረስ እቆያለሁ።" መድረክ ላይ ለሰምንት ቀን እና ሌሊት ቆየሁ፡ አያችሁ። ከዚያም... ከክፍሉ ጥግ አንዲት ሴት ወጣች። መሀረቧን **እንደዚህ** ሸፍናው ነብር፡ እና እያለቀሰች መሰለኝ። እኔም አልኳት... እና፡ ከጠዋቱ ሁለት ወይም ሶስት ሰዓት ይመስለኛል፡ "አታልቅሺ፡ እህቴ፡ የሚፈውሰው እግዚአብሔር ነው፡" አልኳት።

337 እንዲህ አለች፡ "እያለቀስኩ አይደለም፡ ወንድም ብራንሃም።" ሰትገልጠው፡ አፍንጫ አልነበራትም፡ አያችሁ። ዶክተሮቹ እንደተናገሩት... ካንሰሩ በእሷ ውስጥ እስከ ነጭ አጥንቷ ድረስ በልቷታል... ብለው አሳይተዋል። እኔም ጸለይኩላት፡ እንዲፈውሳትም ጌታን ለመንኩላት።

338 ከዚያ ከአራት ወይም አምስት ሳምንታት በኋላ፡ በቴክሳርካና ውስጥ ነበርኩ። በዚያም በጥሩ የጨዋ ሰው ልብሰ-ለብሶ የተቀመጠ ሰውዬ ነበር፡ እንዲህም አለ፡ "ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ አንድ ቃል ብቻ ልናገር? "

339 ወደ‚ያው መድረኩ ላይ እንደወጣ፡ ከአሰተናጋጆች አንዱ ዝም እንዲል ለማድረግ ሞከረ። እኔም "እስኪ፡ እንየው፡" አልኳቸው።

340 እንዲህም አለ፡ "ይህችን ወጣት እመቤት ታስታውሳታለህን? "

341 "አይ፡ አላስታወስኳትም፡" አልኩት።

342 እሷም "ይህን ምስል ከተመለከትከው ታስታውሳለህ፡" አለችኝ። ሰውዬው በ—በቴክሳርካና ውስጥ እንስሶችን የማሰወገድ ስራ የሚሰራ ነበረ፡ ይህች አዲስ-አፍንጫ የበቀለላትም እናቱ ነበረች፡ ልክ እንደሌላኛው በትክክለኛ ቅርጽ ነበረ።

343 እንግዲህ ይህ የሚያሳየው... እኔ ራሴ ሲፈጸም አይቼዋለሁ። አሁንም፡ እግዚ አብሔር ለምስኪኗ ለወይዘሮ ሃርቪ ይህ ሊያደርግላት ይቻለዋል። እና ይህን እንዲያደርግላት ጸሎቴ ነው፡ ምስኪኗ መኖር ትፈልጋለችና።

344 ወንድም ቶኒ፡ የምትለው ነገር አለህ?

[ወንድም ቶኒ የፈውስ ምስክርነት ተናገረ—አርታዒ።] ልክ ነው።

ኣሜን። ኣሜን። አዎን፡ ያ ደግሞ፡ መልካም ነው። አዎን፡ እሱ በእርግጥ ያደርገዋል፡ ፈዋሽ ነውና።

[አንድ ወንድም ወንድም ብራንሃምን አነጋገረው—አርታዒ።] አዎን። አዎን። አዎን፡ ወንድሜ። ኣሜን። በትክክል። አዎን።

345 እርግጠኛ ሆኜ... መልካም፡ ልጄ ሆይ፡ እግዚአብሔር ይመልሰልህ ዘንድ ተሰፋ አደርጋለሁ፡ እንደገና እምጥተህ ልታሳየው ትችላለህ። በትክክል ልክ ነው። ለእግዚአብሔር ክብር ምስክር ነው፡ እግዚአብሔር እንዲያደርገው

ጸልዩ። ኦህ፡ እ—እ... ሁሉን ቻይ አምላክ ከሆነ፡ ሁሉንም ነገር ማድረግ ይችላል። ሁሉን ነገር፡ ማድረግ ካልቻለ፡ ሁሉን ቻይ አምላክ አይደለም።

346 አሁን ባለንበት ሁኔታ፡ እንድንሆን ያደረገን አንድ ነገር አለ፡ እኛ ሁላችንም አሁን ባለንበት ሁኔታ—መሆን እንድንችል ያደረገ፡ ጥበበኛ አካል፡ ከበስተጀርባ ባይኖር ኖሮ እንደ ወፍ ያለ ጭንቅላት ወይም እንደዚህ ያለ ነገር በሆንን ነበር፡ የጥድ ዛፍ፡ የፖፕላር ዛፍ፡ የዘንባባ ዛፍ፡ እ—እና በየወገናቸው ልዩነት እንዲኖራቸው—ያደረገ አካል አለ። እኛን እንዲህ አላደረገንም... አንዳንዶቹን ባለ ጸጉር፡ አንዳንዶች ባለ ላባ፡ አንዳንዶችም ባለ ቆዳ፡ ያደረጋችሁ... አያችሁ፡ ከዚህ ሁሉ በስተጀርባ ጥበበኛ አካል አለ፡ ያ—ያንን ሁሉ የመራ እርሱ ነው። በእርግጥ እርሱ ሁሉንም ነገር በእጁ ይይዛል። እና ሁሉንም ነገር ማድረግ እንደሚችል አውቃለሁ። እና እንጸልያለን፡ እንጸልያለን።

347 [አንድ ወንድም ወንድም ብራንሃምን አነጋገረው—አርታዒ።] ትክክል። አለ...

348 [እህት ሰናይደር "ወንድም ቢሊ፡ ይቅርታ አድርግልኝ፡" አለች።—አርታዒ።] እሺ፡ እመቤት፡ ምንም አይደለም፡ ቀጥዪ። [እህት ሰናይደር ባለፈው እሁድ ወንድም ብራንሃም ሲጸልይላት እንደዳነች መሰከረች።] አሜን። ታውቃላችሁ፡ አንድ ቀን፡ እዚህ መድረክ ላይ በቅባት ስር ሆኜ፡ ስለ እህት ሲንደር ለማሰብ ሞከርኩኝ፡ እንዲህ አሰብኩ... ወንድም ኮክስን ነግሬዋለሁ፡ እንዲህ አልኩት፡ "በዚህ ተበርናክል ውስጥ በሚደረጉ ሰብሰባዎች የማደርጋቸውን የመለየት አገልግሎቶች ከእንግዲህ አልሞክራቸውም።" ኦህ፡ ያ ሰይጣን ጉባኤው ላይ እንዴት እንደሚነክሰኝ አታውቂም፡ እህቴ። እንዴት—እንዴት ያደርገዋል! ታውቃላችሁ፡ ስለ እነዚህ መለየቶች ሲነግርኝ።

349 እና እዚህ ጋር፡ የወይዘሮ ውድ እህት እዚህ እንዳለች ለማወቅ ቻልኩኝ... ከዘመዶቻቸው አንድም አይቼ አላውቅም ነበር። ብዙዎቻቸው፡ እና ሁሉም ያን ጊዜ ነበር የተፈወሱት... ለምን፡ ታውቃላችሁ፡ ከሰዎቹ መካከል አብዛኞቻቸው ተፈውሰዋል። እና በኋላ... የሚገርመው አሁን፡ እህቷ፡ ከዚያ ከሁለት ሳምንት በፊት፡ አንድ ምሽት ከእርሷ ጋር እራት በልቼ ነበር፡... ኦህ፡ ከኬንታኪ ተራሮች ወደ ታች ይወርዳል፡ እና ድምጿ ልክ—እንደ ወይዘሮ ውድ ያለ ድምጽ እንዳላት አውቃለሁ፡ እና በክፍሉ ውስጥ በጣም ቀላል አልነበረም። እና በበለጠ፡ ከባለቤቷ ጋር እያወራሁ ስለነበረ፡ ምንም አይነት ትኩረት አልሰጠኋትም ነበር፡ እራትም አዘጋጀች። ወጥተንም ተቀምጠን በላን፥ ተመልሼ ገባሁ፡ ከባለቤቷ ጋር አወራን፡ ተነስቼ ወጣሁ። እና ዳኛዬ የሆነው አምላኬ ያውቃል (በዚህ መድረክ ላይ ቆሜአለሁና) ያቺን ሴት በጭራሽ ትዝ አላስታውሳትም።

350 እናም የፈውስ አገልግሎት ካለቀ በኋላ፡ ኃጢአተኞች ንስሐ እንዲገቡ የመሠዊያው ጥሪ አደረግሁ። እና በዚህ ነገር ላይ እጅግ ተቃዋሚ የነበረች፡ ንስሐ ገብታ ህይወቷን ለክርስቶስ ሰጠች፡ ሕይወቷን ለክርስቶስ አሳልፋ እንድትሰጥ እጇን ከፍ አርጋ፡ እያለቀሰች ነበር። የመሠዊያዬን ጥሪ አድርጌ፡ ወዘተ፡ ቅባቱ ለቆኝ ነበር። እናም በአጋጣሚ ተመለስኩ፡ እና እነሆ ራእይ አየሁ፡ እናም ወንድሟን አየሁት፥ እርሰዋም እኅቱ ነበረች፡ ይህች እህቱ ነበረች፡ ሁሉም በአንድነት።

351 እና የቻርሊ ሚስት መስላኝ ነበር፡ ምክንያቱም ባለፈው ቀን ጠረጴዛው ላይ ቁጭ ብለን፡ እዚያ እነ ቻርሊ ቤት—ተቀምጠን ሳለ... ስለ ምስኪኗ ሚስቱ፡ ምስኪን ነገር ናትና፡ ጌታ ያጋጠማትን ችግር አሳይቶኛል። ከዚያች ሰዓትም ጀምሮ፡ ጌታ ሥጋዋን ዳሰሰ፡ አሁን ይኸው ጠረጴዛዋ ላይ ቁጭ ብላለች። ቶኒ፡ ያኔ በነበርንበት፡ እዚያ፡ ሽኮኮን ለማደን ወጥተን ነበር። ጌታም ሰውነቷን ዳሰሰ እና... ለቀሪ ዘመኗ ሰውነቷ ላይ ያለበሳትን ነገር፡ ከላይዋ ላይ አስወገደላት፥ ይኸው ቁጭ ብላለች። እና ሁልጊዜ በጠረጴዛው በሌላኛው ጫፍ ላይ ትቀመጥ የነበረችው፡ ይህች ምስኪን ሴት፡ አሁን ግን ወንድበሯን ጠጋ አድርጋ፡ ወዲህ ቀረበች፡ እና አጠገቤ ሆና ተመገበች። ምን እየሰራች እንደነበረ አልገባትም። ባለቤቷ **እንደዚህ** ቁጭ ብሎ ነበር፡ ወንድም ባንክስ ደግሞ እዚያ ጋር ቁጭ ብሏል፡ እያወራን ነበር። እናም ተንቀሳቀሰችና፡ ወንበሯን ያዘች፡ እዚህ ከጎኔ አስቀመጠችው። ለዓላማም ነበር፡ ጌታ እዚያው እንዳለ ራእይ አሳየኝ። እና ባሏን ጠራሁት፡ የሴት ችግር ስለሆነ፡ ስለተፈጠረው ነገር መንገር ጀመርኩ። እንዲህም አለ፡ “ወንድም ብራንሃም፡ ልክ ነው፡ የሆነው ልክ እንደዛ ነው።” ያን ጊዜ እሱም ነገራት፡ ጌታም ፈወሳት። በጣም ጥሩ።

352 እና በቀደም ማታ አገልግሎቱ ከተጠናቀቀ በኋላ፡ እና ይህች ሌላዋ እህት፡ ወጣት ቻርልስ እና ይህችን ሴት አንድ ላይ አይቻቸዋለሁ። እኔም “ሚስቱ ናትን፥ ሚስቱ ባለ ወርቃማ ጸጉር ናት፡ ይህች ግን ባለ ጥቁር-ጸጉር ሴት ነች፡” ብዬ አሰብኩ። እናም በአጋጣሚ ራእዩ እዚህ ጥግ ላይ ሲንቀሳቀስ አስተዋልኩ። ወደዚያም ተቀምጣ አይኖቿን እየጠረገች ነበረች እና ከዚያ በኋላ ጌታ ራእይን አሳየኝ... ከመሠዊያው ጥሪ በኋላ... የጸሎቱ ስብሰባ ካለቀ በኋላ፡ የታመሙ ሰዎች ፈውስ በኋላ፡ እና የመሠዊያው ጥሪ ተደርጎ ነበር፡ እግዚአብሔርም ንስሐ ገብታ ህይወቷን ለእርሱ እስክትሰጥ ድረስ ከዚያም እንዲፈውሳት ጠበቀ። እና የነበረባት... ችግር ለአመታት አብጦ የቆየ ነገር ነው። እና ሁሉም ከእርሷ አልፎ፡ እግሮቿ እስኪጨማደዱ ድረስ፡ እና ሁሉም ነገር ወደ ታች (መርዞቹ) ከሰውነቷ ውስጥ ወደ ታች ወርዷል። አሁን ለዓመታት ይሰማት ከነበረው የተሻለ ስሜት ይሰማታል፡ አያችሁ። አቤት ጌታ አሰራሩ በአስደናቂው ጸጋው ይህን እንዴት አደረገ! እኔ እንደማስበው ታሪኩ ነው፥ አይደል፡ እህት ውድ? አቤት ሲሰራ! ም... ምን አልሺኝ? [እህት ውድ እንዲህ አለች፡ “ባለፈው ሳምንት ሰባት ፓውንድ ቀንሳለች።”—አርታዒ።] በሳምንት ውስጥ ሰባት ፓውንድ። ኧረ፡ እሱ አምላክ ነው፡ አይደል?

353 አሁን፡ ለወንድም ኔቪል ያልኩትን፡ ምክንያት እነግራችኋለሁ... ምናልባት ለዛሬ ምሽት መልእክት አለው ብዬ አሰቤ ነበር። እርሱም፡ “አይ፡” የለኝም አለ። እና እዚህ የቀሩ ጥቂት ጥያቄዎች አሉኝ፡ ወደዚህ ወርጄ ለጥያቄዎቹ መልሰ ለመስጠት የሞራል ግዴታ እንዳለብኝ ተሰማኝ። ከዚያ ሁለት ወይም ሶስት ተጨማሪ አሉኝ ምናልባት ዛሬ ማታ ላልዳሰሳቸው እችላለሁ።

354 የተወሰኑትን ላሳያችሁ እፈልጋለሁ ከሰባኪ የተሰጡኝ ናቸው። ወንድም ኔቪል፡ ወይም፡ ቢለር ወደ እኔ አምጥቷቸዋል። [ወንድም ብራንሃም የሚከተሉትን ሰምንት ጥያቄዎች በክፍል III፡ ከጥያቄ ቁጥር 67 እስከ 74 መልስ ሰጠ—አርታዒ።]

**በራእይ 21:19 እና 20 ላይ ያሉት ድንጋዮች ምን ያመለክታሉ?**

**በራዕይ 5 ላይ ያሉትን አራቱን እንስሶች አስረዳን...** 6 ላይ ማለቱ ነው፥ ራእይ 5፡ ሳይሆን 6 ነው፡ ይመስለኛል።

**እና ሃያ-አራቱ ሽማግሌዎች እነማን ናቸው?**

**በዘፍጥረት 38 ላይ ያለው ቀይ ክር ምን ማለት ነው?**

**የሁለቱ ምስክሮች ሞትን በተመለከተ፡ በራዕይ 11 ላይ የሚላላኩ ስጦታዎች የት አሉ?**

**ከሺህ-ዓመት መንግስት በኋላ ቅዱሳን የት ይሆናሉ? ምን ዓይነት አካልስ ይኖራቸዋል?**

**በመላእክት እንዴት እንፈርዳለን?**

**በአንደኛ ቆሮንቶስ ያለው ጸጉር ለመላእክት ምናቸው ነው?**

355 ጥሩ ጥሩዎቹን ካላችሁ፡ ጥሩ ጥሩዎቹ እነዚህ ናቸው። ምናልባት ዛሬ ማታ ላልጨርሳቸው እችላለሁ፡ ጌታ ቢፈቅድ ግን፡ ለዛ ስንመጣ በሚቀጥለው ጊዜ ላገኛቸው እሞክራለሁ።

356 ዛሬ ማታ አንዳንድ ጥሩ ሰዎች አሉን፥ ስለዚህ አሁን እንጸልያለን ጌታም እንዲረዳን እንለምነዋለን፡ እና ለሚቀጥሉት፡ ኦህ፡ ምናልባት ሠላሳ-አምስት፡ አርባ ደቂቃዎች ወደ እነርሱ እናልፋለን።

357 አሁንም፡ ብሩክ የሰማይ አባት ሆይ፡ ስላደረግክልን ነገር ሁሉ እናመሰግንሃለን። እናም፡ አቤቱ፡ ግሩም ጸጋህ ወደ እኛ እንዴት እንደደረሰ በጣም ያስደንቃል። አሁንም አስባለሁ፡ በቀደም ማታ ላይ፡ ኦህ፡ ምስኪኗ ባለቤቴ፡ እጅግ ታማ ነበረች፡ አንተም ደረስክላት። ትኩሳቱ ከዚያ ሰአት ጀምሮ መቀነስ ጀመረ፡ አሁንም ሙሉ በሙሉ ቆሟል። አመሰግንሃለሁ። ስለዚህ... ከእያንዳንዳቸው ጋር እንድትሆን እና ልመና ካላቸው ጋር እንድትሆን እጸልያለሁ። እናም ነገሮች ወደ ቤታችን እስኪመጡ ድረስ፡ ትንሿ ጸሎት፡ ምን ማለት እንደሆነች፡ ብዙ አይገባንም። አምላክ ሆይ፡ አቤቱ... አንተ—ህያው ሆነህልናል። ሐኪም፡ "እኔ አላውቅም፡ ማንም እንዲህ ሲሆን አይቼ አላውቅም፡" ብሎ ትቶ በሚሄድበት ሁኔታ፡ ጌታ ኢየሱስ ወደ ሰፍራው ከተፍ ይላልና።

358 አምላክ ሆይ፡ አንተ ለእኛ በጣም እውነት ነህ፡እኛም በዚህ በጣም ደስተኞች ነን። የሰነፍ እና የሞኝ መንገዳችንን፡ ይቅር እንድትለን እንጸልያለን። እናም፡ ኦህ፡ ጌታ ሆይ፡ በጨለማ ዓለም፡ በጨለማ እና በኃጢአት እና በግርግር ዓለም ውስጥ የምንኖር፡ ሥጋ መሆናችንን አስብ። እኛም በፊታችን እንደተደረገ መጋረጃ፡ በመጋረጃው ውስጥ ሆነን፡ እየተመለከትን ነው፡ ይህም የምናየው እና የምናውቀውም እንደ ሰው ሰናደርግ ብቻ ነው። አንድ ቀን መጋረጃው ሲነሳ ግን፡ ፊት ለፊት እናይሃለን እንደታወቅነም እናውቃለን። የምንናፍቀው ቀን ነው።

359 እንደ ጥያቄያቸውም፡ የእግዚአብሔርን ቃል ለሰዎች ለማካፈል ስንሞክር፡ አሁንም፡ እንድትረዳን አባት ሆይ እንጸልያለን። በሽታ ሁሉ ከእኛ አሰወግድ። ጌታ ሆይ፡ እንፈልግሃለን። ይህ እንድታደርግ እንጸልያለን። በኢየሱስ ሰም ስለጠየቅን፡ ምህረትህ ይሰጠን። ኣሜን።

360 አሁን፡ ለጥያቄዎች መልስ በመስጠት ረገድ፡ በአገሪቱ ውስጥ ምርጡ እኔ አይደለሁም፡ ታውቃላችሁ። እኔ ግን የማውቀውን ያህል ብቻ እመልሳለሁ።

361 በቀደም ምሽት ጀምሬው፡ እንዳቆመው የተገደድኩት ይህ ነው፥

60. **“በአንድ መንፈስ ሁላችንም የክርስቶስን አካል እንድንሆን ተጠምቀናል።”** (ሁላችሁም የምታስታውሱት እዚህ ጥያቄ ላይ ነበር የደረስኩት። ይህም፡ በርግጥ፡ በአንደኛ ቆርጦስ 12 ላይ የሚገኝ ነው)… **እንዲህ የሚሆነው… አዲስ ልደት ስንቀበል፡ እንዲህ ይሆናል። እንዲህ ነው… የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ነውን፡ ወይስ ኋላኛው ጥምቀት አለ፡ ወይንስ መሞላት ነውን?**

362 አሁን፡ አንድ ጥያቄ ነው፡ ይሁን እንጂ ዛሬ ማታ እና ነገ ምሽትም ይሁን ወዘተ፡ የቀረውን ጊዜያችንን በዚሁ ላይ ልናጠፋው እንችላለን። ይህም… መላውን መጽሀፍ ቅዱስን በማስተሳሰር—አንድ ላይ ማጠቃለል የሚችል ነው። ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉት ሁሉም ቅዱሳት መጻሕፍት ጋር በትክክል መያያዝ አለባቸው።

363 ግን ሁሌም እንደማደረገው፡ በአጭሩ ግልጽ ለማድረግ እሞክራለሁ፡ እንደዚያ አይደለም፥ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስታምኑ፡ ያን ጊዜ አዲስ ልደት ታገኛላችሁ። በጌታ ስታምኑ፡ አዲስ ሀሳብ፡ አዲስ ህይወት ትቀበላላችሁ፡ ይህ ግን የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አይደለም። እያችሁ? ባመናችሁ ጊዜ አዲስ ልደት አግኝቹኋል፡ የዘላለም ሕይወት አግኝታቹኋል። እግዚአብሔር የሚሰጣችሁን ስጦታ በመቀበል በሉዓላዊ ፀጋ የሚሰጥህ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው። “ቃ—ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን፡ የዘላለም ሕይወት አለው።” የዘላለም ሕይወት አለው፥ ያ አዲስ ልደት ነው፡ ተለውጣችኋል፡ ይህ ማለት “ተመልሳችኋል” ማለት ነው።

364 የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ግን፡ ለአገልግሎት ስጦታዎች ተገዢ በመሆን ወደ ክርስቶስ አካል ያስገባችኋል። ወደ ስጦታዎች አካል ውስጥ ያስገባችኋል እንጂ፡ ከአሁን በኋላ ክርስቲያን እያደርጋችሁም። እያችሁ? “አሁን፡ በአንድ መንፈስ” (አንደኛ ቆሮንቶስ ሰዎች 12) “ሁላችንም አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናል። ይላል፡” ጳውሎስ ብሏል፡ “ልዩ ልዩ ስጦታዎች አሉ፡ በዚህ አካል ውስጥ ዘጠኝ መንፈሳዊ ስጦታዎች አሉ።” እና በዚህ አካል ውስጥ… ከእነዚህ ስጦታዎች አንዱን ለማግኘት ወደ አካሉ መጠመቅ አለባችሁ። ከአካሉ ጋር ይመጣሉና።

365 ነገር ግን፡ አሁን፡ የዘላለም ህይወት እና ክርስቲያን መሆንን በተመለከተ፡ ባመናችሁ ቅጽበት ክርስቲያን ናችሁ። እንግዲህ፡ አስመሣይ-እምነት አይደለም፡ በእውነት ጌታ ኢየሱስን ማመን እና እንደ ግል አዳኛችሁ በመቀበል ነው፥ ዳግመኛ የተወለዳችሁት ያኔ ነው፡ እናም የዘላለም ሕይወት አላችሁ። እግዚአብሔር ወደ እንተ ይገባል።

366 አሁን ተመልከቱ፡ የዘላለም ሕይወት፥ ኢየሱስም እንዲህ አለ፡ “ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን፡ የዘላለም ሕይወት አለው፡ ከሞትም ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም።” ያኔ አዲስ ፍጥረት ናችሁ። ከዚያም ጳውሎስ በሐዋርያት ሥራ 19 ላይ፡ አንዳንድ ሰዎች አገኘ። በዚያም አጵሎስ የተባለ ከሕግ አዋቂነት የተለወጠ ሰባኪ ነበራቸው። አጵሎስም በመጻሕፍት እውቀት የበረታ ሰው ነበረ፡ ኢየሱስም እርሱ ክርስቶስ እንደ ሆነ በመጻሕፍት ይመሰክር ነበር። እያችሁ?

367 አሁን ተመልከቱ። አጵሎስ፡ በቃሉ፡ በቃሉ አረጋግጧል። “እምነት ከመስማት ነው፡ ቃሉን መስማት ነው። ቃሌን የሚሰማ፡ የላከኝንም የሚያምን፡ የዘላለም ሕይወት አለው።” ገባችሁ? አጵሎስ፡ በቃሉ፡ አረጋግጧል። እነዚህም ክርስቲያኖችም፡ ተከታዮች፡ ደቀመዛሙርት ነበሩ። አጵሎስም ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደ ሆነ፡ በቃሉ ያረጋግጥላቸው ነበር። ታላቅ ደስታም ነበራቸው፡ የዮሐንስንም ጥምቀት ብቻ እያወቁ ቃሉን ተቀበሉ።

368 ጳውሎስም በኤፌሶን በላይኛው አገር አልፎ፡ እነዚህን ደቀ መዛሙርት አግኝቶ ጠየቃቸው፡ “ካመናችሁ **በኋላ** መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን?” አያችሁ?

369 አሁን፡ ባመናችሁ ጊዜ፡ ኢየሱስ እንዳለ፡ “የዘላለም ሕይወት አላችሁ።” አዲስ ልደት ማለት ይህ ነው። የእናንተ መለወጥ፡ መቀየራችሁ ይህ ነው። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ግን የተጠመቃችሁበት እና በእናንተ በኩል ለመስራት ለእነዚህ ዘጠኝ መንፈሳዊ ስጦታዎች ባለ መብት ለመሆን የእግዚአብሔር ኃይል ነው፥ እነዚህም፡ ሰብከት፡ ወንጌላውያን፡ ሐዋርያት፡ ፓስተሮች፡ ነቢያት፡... እና ወደዚህ አካል ስትጠመቁ፡ የጸጋ ስጦታዎች ሁሉ ወደዚህ አካል ይመጣሉ። ይህ ደግሞ... ሌላ ክርስቲያን እያደርጋችሁም፡ በህያው እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ውስጥ የአገልግሎት መንፈስ እንዲኖራችሁ በትክክለኛ ሰፍራችሁ ያስቀምጣችኋል እንጂ። አሁንስ ገባችሁ? አያችሁት?

370 አሁን ጥያቄው... አንድ በአንድ እንመልሳቸው፡ ሶስት ጥያቄዎች አሉ።

**“በአንድ መንፈስ ሁላችንም የክርስቶስን አካል እንድንሆን ተጠምቀናል።”**

ትክክል ነው፡ አንደኛ ቆሮንቶስ 12 መልሱን ይሰጣል። እሺ።

**በዚያን ጊዜ አዲስ ልደትን እንቀበላለን፡ ይህ ይከናወናል? መቼ ነው?**

371 ማወቅ የፈለጉት ያ ነው፡ አይደል... “በአንድ መንፈስ... ” አይደለም። አይደለም። “በአንድ መንፈስ አንድ አካል ለመሆን ተጠምቀናል።” አያችሁ፡ አዲስ ልደት የሚጀምረው ያኔ አይደለም፡ አዲሱ ልደት የሚጀምረው በጌታ በኢየሱስ **ስታምኑ** ነው።

372 አሁን ተመልከቱ፡ እንዲህ... አይነት ነገር የለም... አሁን አዳምጡ። ከማመን በተጨማሪ ምን ማድረግ ይቻላቹኋል? ከዚህ በላይ ምን ማድረግ ትችላላችሁ? ከማመን የበለጠ ምን ማድረግ ትችላላችሁ? እስኪ ማድረግ የምትችሉትን አንድ ነገር ንገሩኝ። ከማመን ውጭ ልታደርጉት የምትችሉት አንድም ነገር የለም። አሁን፡ ከማመን ሌላ የሆነ ነገር ከመጣ፡ የራሳችሁ ድርጊት ሳይሆን፡ የእግዚአብሔር ተግባር ነው። ስለዚህ...

373 አሁን ለምሳሌ እንዲህ ሆነ ብንል... ብዙ ጊዜ አይቻለሁ፡ በተደጋጋሚ፡ ሰዎች “በልሳን መናገርን የመጀመሪያ ማስረጃ” እንደ መንፈስ ቅዱስ አድርገው ሲቀበሉ አይቻለሁ። እና አንዳንዴ ሰዎችን፡ እየደበደቧቸው፡ “ተናገር። ተናገር። ተናገር። ተናገር፡” ይሏቸዋል። ገብቷችኋል፡ አንዲት ቃል ደግጋግመው ለማለት፡ “ተናገር። ተናገር። ተናገር።” አያችሁ፡ እናንተ ራሳችሁ የምትሉት ነገር ነው። እ—እ—እና አይሰራም... አይሰራም... ተ—ተራ ነው። ምናልባት የቋንቋ ግራ መጋባት ሊያጋጥማችሁ ይችላል። ብ—ብዙ ነገሮች፡ እና ስሜቶች

ሊያጋጥማችሁ ይችላል። ነገር ግን ከራስ እምነት ውጭ የሆነ ነገር ከመጣ፡ ለእናንተ የተሰጠ መለኮታዊ ስጦታ መሆን አለበት። አያችሁ?

374 "በአንድ መንፈስም አንድ አካል ለመሆን ተጠምቀናል።" ትክክል ነው፡ አያችሁ። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ከአዲስ ልደት የተለየ ሥራ ነው። አንዱ ልደት፡ አንዱ ጥምቀት ነው። አንዱ የዘላለም ሕይወትን ያመጣልዎታል፡ ሌላኛው ኃይል ይሰጥዎታል። በዘላለም ሕይወት ውስጥ ስልጣን ይሰጣል፡ አያችሁ፡ ለሥራ። አሁን ገባችሁ? እሺ። በጣም ጥሩ።

375 አሁን ሌላኛው እዚህ አለ፡ ሁለተኛውና፡ በዚያ ምሽት ካገኘኋቸው ምርጦች አንዱ ይህ ነው፥

## 61. ሥጋው በመቃብር ውስጥ በነበረ በሶስት ቀናት ውስጥ የኢየሱስ መንፈስ የት ነበር? መንፈሱ የት ነበር?

376 አሁን፡ መንፈሱ፡ መጽሐፍ ቅዱስን የምትከተሉ ከሆናችሁ፡... እሺ፡ ብዙ ስፍራዎችን ማምጣት እንችላለን። ግን፡ እኔ የሚገርመኝ፡ መጽሐፍ ቅዱስ የያዘ ማን አለ? ወንድም ስትሪከር፡ መጽሐፍ ቅዱስ ይዘሃል? እሺ። ወንድም ኔቪል፡ አንተም ይዘሃል? መዝሙረ ዳዊት 16:10 ክፈቱልኝ። ሌላ የያዘ ማን አለ? እህት ውድ፡ መጽሐፍ ቅዱስ አለሽ? እሺ፡ ወንድም ሰቲከር፡ (ወይም፡ አንዳችሁ)፡ ሐዋርያት ሥራ 2፡27፡ የሐዋርያት ሥራ 2፡27 ክፈቱልኝ።

377 አሁን፡ በመጀመሪያው ደረጃ፡ ኢየሱስ ሲሞት... ስትሞቱ፡ አካላችሁ ይሞታል። **ሞት** የሚለው ቃል "መለየት፡" ከወዳጆቻችሁ መለየት ማለት ነው። እዚህ ግን በቅዱስ ዮሐንስ ምዕራፍ 11 ላይ፡ እንዲህ አለ፡ "የሚሰማ... " ቆይ... ይቅርታ አርጉልኝ፥ በቅዱስ ዮሐንስ 5፡24 ላይ ነው፡ "ቃሌን የሚሰማ የዘላለም ሕይወት አለው።"

378 ልትገናኘው የመጣችውን ማርታንን፡ ኢየሱስ እንዲህ አላት፡... እሷም አለችው፡ "አንተ እዚህ ብትሆን ኖሮ፡ ወንድሜ ባልሞተ ነበር። አሁንም ግን፡ እግዚአብሔርን የምትለምነውን ሁሉ፡ እግዚአብሔር ይሰጥሃል።"

379 እርሱም፡ "ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ" አላት። አያችሁ? "በእኔ የሚያምን፡ ቢሞት እንኳ፡ ሕያው ይሆናል፥ ሕያው የሆነም የሚያምንብኝም ሁሉ፡ ለዘላለም አይሞትም።"

380 አሁን—አሁን፡ የማይሞት ክፍል አለን። እና አሁንም እንደመጽሐፍ ቅዱስ ሂደት እንደመጣሁ ሁሉ፡ መጀመሪያ ያለው ሁሉ መጨረሻም አለው። መጀመሪያ የሌላቸው ነገሮች፡ መጨረሻም የሌላቸው ነገሮች ናቸው። ስለዚህ ክርስቶስን፡ አምላክን ስንቀበል፡ የእግዚአብሔር ወንዶች ልጆችና ሴቶች ልጆች እንሆናለን፡ ሕይወታችንም ልክ እንደ እግዚአብሔር ሕይወት ማለቂያ የሌለው ነው፥ ዘላለማዊነት አለን።

381 አሁን፡ **forever** የሚለው ቃል፡ ከዚህ በፊት ተምረነዋል። **forever** የሚል ቃል "የጊዜ ገደብ አለው፡" forever **አንድ** (መስተጻምር) ፎርኤቨር። እና እንደተማርነውም—ልክ እንደ ስቃይ ሁሉ፡ እንደ ህመም ሁሉ፡ እንደ ሃዘን ሁሉ፡ እና እንደ ቅጣት ሁሉ፡ እና ገሃነምን ሁሉ መጨረሻ እንዳለው ሁሉ፡ መጨረሻ ያለው ነገር ነው።

382 የዘላለም ሕይወት ግን መጨረሻ የለውም፡ ምክንያቱም መጀመሪያ ስለሌለው። ስላልተወለደ ፈጽሞ ሊሞት አይችልም። የቀናቶች መጀመሪያ አልነበረውም፡ የጊዜ ፍጻሜም የለውም። ስለዚህ፡ ለዘላለም መኖር የምንችልበት ብቸኛው መንገድ፡ ዘላለማዊ የሆነውን ነገር በመቀበል ነው። እግዚአብሔርም ነበረ፥ ምንም ነገር ከመኖሩ በፊት፡ እግዚአብሔር ነበረ። እግዚአብሔር መጀመሪያም መጨረሻም አልነበረውም።

383 እግዚአብሔርም ታላቅ መንፈስ ነበር። እርሱንም ሁሉን የሚሞላውን—ባለ ሰባት ቀለማት ቀስተደመና አይነት አድርገን መስለነው ነበር… ቀስቱ ምድርን ስለማይነካ እንጂ በእርግጥ ምድርን ይሸፍን ነበር። ይህ እንዲሆን የሚያደርገው፡ በምድር ኩርባ ክብ ውስጥ ያለ ውሃ ነው። ነገር ግን፡ አሁን፡ እግዚአብሔርም ዘላለማዊ ሲሆን ሳለ፡ እንዲሁም ፍጹም ነው፡ ፍጹም ፍቅር፡ ፍጹም ሰላም፡ ፍጹም ደስታ፡ ፍጹም እርካታ ነው። እነዚያ ሲወጡ የምናያቸው (በራዕይ ውስጥ እንደምናገኛቸው)፡ ሰባት መናፍስት ሁሉ፥ የእግዚአብሔርን ፍጹምነት፡ የሚያጎሉ ናቸው። ከዚያ ውጭ ያለው ነገር ሁሉ ከዚያ የተሰረቀ ነው።

384 አሁን ወደ ፍፁምነት የምንመለሰበት ብቸኛው መንገድ፡ ወደዛ (ፍጽምና፡ ማለትም እግዚአብሔር) በመመለስ ነው። ከዚያም ወደ ፍጽምና እንደርሳለን፡ ያኔ የዘላለም ሕይወት እናገኛለን፥ ፍጻሜ የሌለው፡ ወይም ምንም—የሌለው፡ የዘላለም ሕይወት ብቻ ነው።

385 አሁን ስለ ነፍስ… ስለ መንፈስ እየተናገረ ነው። ለዚህ አካል፡ ሰውነታችንን በቅዱሳኑ መቃብር ላይ እናኖራለንና። እና አካሉ… በመጀመሪያ ደረጃ፡ እግዚአብሔር፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ የወጣ ሎጎስ…

386 ወይም፡ እንደነገርኳችሁም፡ ካቶሊካውያን "የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ልጅነት፡" በማለት ይጠሩታል። ይህም፡ ከዚህ ቀደም እንዳልኩት፡ ቃሉ ራሱ ትርጉም አይሰጥም። እያችሁ፡ ዘላለማዊ ልጅ ሊኖር አይችልም፡ ምክንያቱም ልጅ መጀመሪያ ስላለው። ስለዚህም ኢየሱስም መጀመሪያ ነበረው፡ እግዚአብሔር መጀመሪያ አልነበረውም። እያችሁ? ልጅ ግን ነበረው… ዘላለማዊ ልጅነት ሳይሆን፡ በመጀመሪያ ከአብ ጋር የነበረው ልጅ ግን ከእግዚአብሔር የወጣ ሎጎስ ነበረ።

387 የወጣውም የእግዚአብሔር ቲዮፋኒም እርሱ ነበር። እንደምታዩት ዓይን ሳይሆን፡ የተሻለ ዓይን የነበረው የሰው አምሣል። እናንተ እንደምትሰሙበት አይነት ጆሮ ሳይሆን፡ ከዚያ በበለጠ መሰማት የሚችል። እያችሁ፡ ቲኦፋኒ ነበረ፡ ማለት፡ ይህ ቀስተ ደመና በሙላት ወደ—ቲኦፋኒ ውስጥ ገባ። ሙሴም እንዲሁ በዓለት ውስጥ ሲያልፍ አይቶታል። ጀርባውን አይቶ፡ "ሰው ይመስላል፡" አለ።

388 አብርሃምም በሰው ሥጋ በተገለጠ ጊዜ ጥጃን በልቶ፡ ወተት ጠጥቶ፡ ቅቤውን በበላ ጊዜ አይቶታል። አብርሃም ገና ሲገባ አየው፡ እና ከዚያ ወዲያው ከሱ ተሰወረበት። ሰውነታችን ከአሰራ ሰድሰት የምድር ንጥረ ነገሮች የተሠራ መሆኑን አውቀናል፡ እነዚያም የተሰሩ ናቸው። እግዚአብሔርም ሰራቸው፡ እና በእነዚህም አካላት ውስጥ ሁለት መላእክትን አኖረ፥ ቆመው የሚናገሩ መላእክት። መላእክቱም በቅጽበት ሰዎች ሆኑ… ይህም ያኔ የሆነ ነገር ነው።

389 እንግዲህ እናስተውል፡ እርሱንም እንዳወቅነው፡ መልከ ጼዴቅ ነበር እግዚአብሔር ራሱ ነበር! እሱም የሳሌም ማለት የኢየሩሳሌም ንጉሥ ነበርና፡

ከሱ ሌላ ማንም ሊሆን አይችልም። አባትና እናት አልነበረውም፥ አባትና እናት ስለነበረው፡ ይህ ኢየሱስ ሊሆን አይችልም። ለዘመኑ መጀመሪያ አልነበረውም፡ ለሕይወትም ፍጻሜ አልነበረውም፥ ያ ያለው አንድ ብቻ ነው፡ እርሱም እግዚአብሔር ነው። ይህም በቲዎፋኒ ውስጥ የሚኖረው እግዚአብሔር ነበር። አያችሁ? አስተውሉ፡ የሳሌም ንጉሥ።

390 አሁን፡ እግዚአብሔር በዘመናት ውስጥ፡ በህዝቡ በኩል ኖሯል። በዳዊት ውስጥ የነበረው፡ በተራራ ላይ ወጥቶ፡ እንደ ተጠላ ንጉሥም እንዲያለቅስ ያደረገው፡ እግዚአብሔር ነበር። ይህ ተመሳሳይ የሆነ የዳዊት ልጅ መንፈስ በኢየሱስ ላይ ተገለጠ፡ እርሱም በኢየሩሳሌም ተጠላ አለቀሰም።

391 ዮሴፍ፡ በሠላሳ ብር ተሸጠ፡ በአባቱ የተወደደ፡ በገዛ ወንድሞቹ ግን ተጠላ፡ በፈርዖን ቀኝ ተቀመጠ፡ ስለዚህም በዮሴፍ በኩል ካልሆነ በቀር… ማንም ሰው በሌላ መንገድ ሊገባ አይቻለውም ነበር፡ መለከት ሲነፋም ጉልበት ሁሉ ለዮሴፍ ይንበረከክ ነበር፡ የክርስቶስ ፍጹም ተምሣሌት ነው። ያም በእነዚያ ሰዎች የሚኖረው የክርስቶስ መንፈስ ነበር። አያችሁ?

392 አሁን፡ እዚህ ጋር ኢየሱስ ሲሞት፡ እርሱ በሥጋ የተገለጠ እግዚአብሔር ነበረ። እግዚአብሔርም ሰው ሆነ። በመዋጀት ሕጎች መሰረት፡ ሰው የጠፋውን የእስራኤልን ግዛት መቤዠት የሚችልበት ብቸኛው መንገድ፡ ዋርሣ በመሆን ነበረ። የቅርብ ዋርሣ ዘመድ መሆን አለበት። መጽሐፈ ሩት በሚያምር ሁኔታ ገልጾታል፥ እና ዋርሣ መሆን ይኖርበታል። ስለዚህ ሰው የእግዚአብሔር ዘመድ ይሆን ዘንድ፡ እግዚአብሔር ለሰው ዘመድ መሆን ነበረበት። አያችሁ?

393 ሰው ሲወለድ፡ በውስጡ መንፈስ አለው፡ ይህ መንፈስም የተፈጥሮ መንፈስ ነው የዓለም መንፈስ ነው፡ የዚህ የዓለም አምላክ—መንፈስ ነው። አዳማዊ ዘር ብቻ ነው።

394 ዛፎች ራሳቸውን ያራባሉ። እፅዋት እራሳቸውን ያራባሉ። እንስሶች እራሳቸውን ያራባሉ። ሰዎችም በራሳቸው ይራባሉ። ከኦሪጂናል ፍጥረት የተገኙ ተረፈ-ምርት ናቸው። ገባችሁ?

395 አሁን፡ ሰው በተወለደ ጊዜ፡ የዚህ ዓለም መንፈስ ይዞ ይወለዳል። እንደገና መወለድ ያለበትም ለዚህ ነው። ይህ መንፈስ ከአባትና ከእናት መፀነስ የሚመጣ ነውና፡ እርሱም ዖታዊ ፅንስ ነው፡ እና በፍጹም ለዘለአለም ሊኖር አይችልም። ስለዚህ ዳግም መወለድ አለበት። እና ይህን መሆን ከመቻሉ በፊት ግን፡ ዳግም መወልድ እንዲችል እግዚአብሔር ወርዶ መንገድ ማመቻቸት ነበረበት፥ ራሱን የሚቤዥበት ምንም መንገድ አልነበረውምና፡ ተስፋ የሌለው ነበር። አልነበረውም… ያለ ተስፋ፡ ያለ እግዚአብሄር፡ ያለ ክርስቶስ፡ በዓለም፡ ጠፍቶ ወድቆም ነበረ። እ—እ… እራሱን የሚያድንበት ምንም ነገር አልነበረውም። ካ… ካህን… ይሁን ማንም፡ ወይም ቢሾፕ ይሁን፡ ወይም ጳጳስ፡ ምንም ይሁን ማን፡ ልክ እንደሌላው ሰው ሁሉ ጥፋተኛ ነው።

396 ስለዚህ፡ ይህን ለማድረግ፡ ጥፋተኛ ያልሆነ አካል መምጣት ነበረበት። ስለዚህ ጥፋተኛ ያልሆነው ብቸኛው እግዚአብሔር ራሱ ነው። እግዚአብሔርም ወርዶ ሰው መሆን ነበረበት (በክርስቶስም መልክ መጣ) የሞትን መውጊያ ለመወጋት፡ የሞትን መውጊያ አውጥቶ፡ ይቤዠን ዘንድ መጣ፡ ይህም… በስራችን እና በመልካምነታችን አይደለም (እንዳች መልካም የለንምና)፡

ነገር ግን በጸጋው፡ ድነናል። ስለዚህ የእርሱ ህይወት ወደ ሟች አካላችንን እንቀበላለን፡ አሁንም የእግዚአብሔር ወንዶች እና ሴቶች ልጆች ሆነናል። የዘላለም ሕይወትም በውስጣችን አለን። እኛ የእግዚአብሔር ወንዶች እና ሴቶች ልጆች ነን። ስለዚህ፡ ኢየሱስ፡ ሕያው ሆኖ...

397 እና ማንም ሰው፡ ምንም ያህል ክፉ ወይም ጥሩ ቢሆን፡ ይህን ምድር ለቆ ሲሄድ... ወይም ሲያልፍ፡ አልሞተም። በሆነ ቦታ ይቆያል። ይህን እንጂ ስለ ክፉ ስራው፡ በገሃነም ከተቀጣ በኋላ የሚጠፋ ህይወት ያለው ነው፡ እ... ያ ህይወት መኖርን ማቆሙ አይቀርም። የዘለአለም ህይወት አንዲት አይነት ብቻ ናትና።

398 እንግዲህ፡ ይህ ተምረነዋል። ለምስሣሌ አንድ ሰው ኃጢአተኛ ተብሎ ለዘለአለም ከተቀጣ... የዘላለም ሕይወት የሌለው ካልሆነ በቀር ለዘለአለም ሊቀጣ አይችልም። የዘለአለም ህይወት ያለው ከሆነ ደግሞ፡ ድኗል ማለት ነዋ። እያችሁ? ስለዚህ አንድ ዓይነት የዘላለም ሕይወት ብቻ አለች፡ ያም **ዞዊ** ይባላል፡ "የእግዚአብሔር ሕይወት" ማለት ነው። ሊጠፋም አይችልም።

399 ክፉዎች ግን—በመጠበቂያ በአንድ ቦታ ላይ ናቸው (በሥቃይ) በመጨረሻው ቀን (በአካል ውስጥ በተደረጉት ድርጊቶች መሠረት) ይፈረድባቸዋል። አሁን ግን፡ እ... የአንዳንድ ሰዎች ኃጢአቶች ይቀድሟቸዋል፡ አንዳንዶቹም ይከተሏቸዋል።

400 አሁን ኃጢአታችንን ብንናዘዝ፡ እርሱ ይቅር ይለናል፡ ስለዚህ መቼም ቢሆን በእግዚአብሔርን ፍርድ መቆም የለብንም ማለት ነው። ገባችሁ? ወደ ሮሜ ሰዎች 8:1 ላይ፡ ተመልከቱ፡ "እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም።" በክርስቶስ ውስጥ ናቸውና። ከሞት ወደ ሕይወት ተሻገረ፥ እያችሁ፡ በክርስቶስ ኢየሱስም ስለነበርን ኩነኔ የለብንም። "በመንፈስ ፈቃድ እንጂ፡ በሥጋ ፈቃድ አይመላለሱም።" እያችሁ? "ቃሌን የሚሰማ፡ የላከኝን የሚያምን፡ የዘላለም ሕይወት አለው።"

401 በክርስቶስም ተቀባይነት ካገኘሁ፡ እና ክርስቶስ ፍርዴን ከወሰደ፡ ለኃጢአቴም ማስተሰረያውን ከተቀበልሁ፡ እግዚአብሔር እንዴት ይፈርድብኛል? በክርስቶስን በፈረደበት ቀን፡ እኔንም ፈርዶብኛል። እንግዲያውስ ከፍርድ ነጻ ነኝ። "ደሙን ሳይ፡ አልፋችኋለሁ።" እያችሁ?

402 አሁን፡ ክፉዎች ግን፡ እንደዚያ አይደሉም። ወደ ሰቃይ ስፍራ ይሄዳሉ። እና ያ እውነት መሆኑን እናውቃለን። ክፉዎች ሕያዋን ናቸው። በስቃይ ስፍራ ይቆያልና። በማያውቀው ስፍራ ይወሰዳል... መናፍስታውያን እና ጠንቋዮች እንዲሁም ሙታን ጠሪዎች፡ አንዳንድ ዋዘኞች እና ቆሻሻ ቀልዶች እና ዕጽ ተጠቃሚዎች ሁሉ እንዲህ ናቸው፡ ምናልባት አይታችሁ የምታውቁ ከሆናችሁ። እሺ። ለምን? እ...

403 **ዘ ሚራክል ኦፍ ዶኒ ሞርቶን** የሚለው ጽሑፌ ከመለቀቁ በፊት የነበረችውን፡ ሚስ ፓይፐርን ተመልከቷት። ያንን ጽሑፍ ያነበባችሁ ስንቶች ኣላችሁ? አዎን፡ ብዙዎቻችሁ፡ አንብባችኋል። በሪደርስ **ዳይጄስት ታገኙታላችሁ።** አስተውላችኋል? ልክ ከዚያ በፊት፡ ሚስ ፓይፐር ወጣች፡ አለም የሚያውቃት ታላቅ ሙታን ጠሪ ናት። ስለ ታሪኳ አስራ ሁለት ገጽ ተጽፎላታል። እና ለሃምሳ አመታት... ሳይንሳዊ ማረጋገጫን ጨምሮ በብዙ ነገር፡ በዓለም ዙሪያ አዙረዋታል፡ ይህም "ከሙታን ጋር ፍጹም እንደምትናገር፡

እና ሰዎቹም እንደሚመጡ ነው።" ምን? የእግዚአብሔር ስም አንድ ጊዜ አልተነሳም፡ ኀሰሃ የለም፡ መለኮታዊ ፈውስ የለም፡ ይሄን በተመለከተ አንዳች ነገር አይነሣም፡ አያችሁ።

404 እነዚያ ሰዎች የተናገሩት፡ ማድረግ የሚችሉት ብቸኛው ነገር፡ "ጆን፡ አታውቀኝምን? መኖሪያዬ እዚህ እና **እዚያ** ቦታ የነበረ ጆርጅ ነኝ፡ እና **ይሄን-እና-ያንን** እንንዲሁም **ይሄን-እና-ያንን** አድርጌ ነበር። ትዝ ይልሃል እዚህ ቦታ ወርደን እንዲህ አርገን ነበርን?" አያችሁ፡ ከዚህ የዘለለ አያውቁም። ጠፍተዋል። አልፎባቸዋል... ከፍርድ በቀር የ—የቀረላቸው ነገር የለም።

405 ዛፉ ዘንበል ባለበት መንገድ፡ የሚወድቅበት በዚያ ነውና። የምትሞቱበት ሁኔታ... በሙታን መጸለይ የምቃወመው ለዚህ ነው፡ አያችሁ፡ የምልጃ ጸሎት ወ—ወይም የቅዱሳን ተራዳኢነት ወዘተረፈ የማልስማማበት ይህ ነው። እንደ እግዚአብሔር ቃል መሰረት፡ ይህ የማይሆን ነገር ነው። ከሞቱ በኋላ በማንም ሰው መጸለይ ምንም አይጠቅምም። ጨርሰዋል። በ... በ... በምህረት እና በፍርድ መካከል ያለውን መሰመር አልፈውታል። ወይ ወደ ምሕረት ሄደዋል፡ ወይም ከምህረት ርቀዋል። በቅዱስ ማቴዎስ ምዕራፍ 16 ላይ፡ ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፡ እ—እ—እንዲህ አስተማረ፥ ማርቆስ ምዕራፍ 16፡ ይመስለኛል። ስለ ባለጠጋው እና አልዓዛር፥ ማንም ሰው በዚህ ገደል መሻገር አይችልም፡ እና በጭራሽ አይሻገሩም! ይኸው ነው። አያችሁ? አራት ነጥብ።

406 አሁን፡ ክርስቶስ ሲሞት ግን፡ ሁሉም ነገር እርሱ ክርስቶስ መሆኑን መሰከረ። አሁን ወደ ጥያቄህ እንለፍ። የመጀመሪያው ነገር፡ ከዋክብት አንበራም አሉ፡ ፀሐይም ገባች፡ ጨረቃ ብርሃኗን አልሰጥም አለች፡ በሞተ ጊዜ የምድር ዓለቶች ተሰነጣጠቁ። በኖኅ ዘመን ትዕግሥት፡ ንሰሐ ላልገቡ በእስር ላሉ ነፍሳት ወርዶ ሰበከላቸው። እርሱንም፡ ማወቅ ይገባቸው ነበር። ያን ተመልከቱት! በአጋጣሚ በዚህ ምሽትም ኃጢአተኛ ካለ፡ ያንን በአንድ ደቂቃ ውስጥ አስቡበት። ይህ አሁን ሲሰበክ የምትሰሙት ወንጌል፡ አንድ ቀን በእርሱ ይመሰከርባችኋል። ምንም ሁን ማን፡ በሆነ ስፍራ ላይ ጉልበት ማንበርከክህ የማይቀር ነው። ምናልባት የዛሬ አስር ሺህ አመት ሊሆን ይችላል፡ ምናልባት... ሳይነጋ በፊትም ሊሆን ይችላል። መቼም ይሁን፡ በሆነ ስፍራ ላይ ትንበረከካላችሁ። ይህ ወንጌል ለእናንተ ተመልሶ ሲሰበክ ትሰሙታላችሁ።

407 ሄኖክና ሌሎች በሰበኩ ጊዜ፡ ንሰሐ ያልገቡ እነዚያ ነፍሳት ታሰረው ነበሩ፡ ኖህም... ያቺ ቀን እስክትመጣ ድረስ፡ ስለ እግዚአብሄር ትዕግስት፡ እንደ አሁኑ ጊዜ ታገሰ። ኖህና ሄኖክም ሌሎችም ሰብከዋል፡ እነዚያም ሰዎች ሳቁባቸውና ተሳለቁባቸው። ስለዚህ በእስር ቤት ቆዩ፡ ኢየሱስም ወርዶ በእስር ለነበሩ ሁሉ ሰበከላቸው። መሰከረባቸው! እርሱ መሆኑን ሰማያት መሰከሩ፡ ምድርም እርሱ እንደ ሆነ መሰከረች፡ ገሃነምም እርሱ እንደ ሆነ መሰከረ።

408 መጽሐፍ ቅዱስ ተናግሯል... ዳዊት፡ ከብዙ ዓመታት በፊት፡ በመዝሙር ላይ... እሺ፡ ወንድሜ፡ ከቻልክ መዝሙረ ዳዊትን እንብብልን። መዝሙረ ዳዊት 16:10። [ወንድም ኔቪል መጽሐፍ ቅዱስን አነበበ—እርታዒ።]

> [**ነፍሴን በሲኦል አትተዋትምና፥ ቅዱስህንም መበስበስን ያይ ዘንድ አትሰጠውም።**]

409 ወንድሜ፡ ጴጥሮስ በሰበከበት፡ ከሐዋርያት ሥራ ላይ፡ ተመሳሳይ ነገር አንብብልን፡ 2ኛው ምዕራፍ፡ 27ኛው ቁጥር። [ወንድም ሰትሪከር መጽሐፍ ቅዱስን አነበበ—አርታዒ።]

**[ነፍሴን በሲኦል አትተዋትምና፡ ቅዱስህንም መበስበስን ያይ ዘንድ አትተወውም።]**

410 አውዱን በደንብ እንድንረዳው፡ ከሱ በላይ ሁለት ጥቅሶችን አንብብ፡ ወንድሜ።

**[ዳዊት ስለ እርሱ ተናግሯልና፡ እግዚአብሔርን ሁልጊዜ በፊቴ አየሁት፡ እንዳልታወክ፡ በቀኜ ነውና።]**

**[ስለዚህ ልቤ ሐሤት አደረገ፡ ምላሴም ሐሤት አደረገ፥ ሥጋዬም ደግሞ በተስፋ ያድራል፥]**

**[ነፍሴን በሲኦል አትተዋትምና፡ ቅዱስህንም መበስበስን ያይ ዘንድ አትተወውም።]**

411 አሁንም የሚቀጥለውን ጥቅስ አንብብ።

**[የሕይወትን መንገድ አሳየኸኝ፥ በፊትህ ደስታን ትሞላኛለህ።]**

412 አዎን፡ አስተውል። አሁን፡ የይሖዋ ምሥክር ጓደኛዬ ሆይ፡ ስለዚህ ጉዳይ ልጠይቅህ እፈልጋለሁ። አየህ? ሲኦል ያ ቦታ ከሆነ፡ ሐዴስ፡ ሲኦል፡ የፈለጋችሁትን ብላችሁ ልትጠሩት ትችላላችሁ፡ ይህ በመቃብር ላይ የሚያበቃ ከሆነ፡ኣንግዲያውስ እንዲህ ለምን ተናገረ፡ "ነፍሴን በሲኦል ውስጥ አልተዋትም፡ ቅዱስህንም መበስበስን ያይ ዘንድ አልሰጠውም"? ይሄስ ታዲያ? አያችሁ?

413 እነሆ ሥጋው፡ በመቃብር ውስጥ ነበር፥ ነፍሱ በሲኦል ውስጥ፡ እየሰበከ ነበር፡ በህይወት! ይሄስ ታዲያ? እንደገና በቲዮፋኒው ውስጥ ነበር። ነፍሱ በዚያ በቲዮፋኒ ውስጥ ካሉት ሰዎች ጋር ነበረች። እርሱም "በትዕግስቱ ውስጥ ንስሓ እንዳልገቡ፡" ይመሰክርባቸው ነበር።

414 እሱም... በሌላ አነጋገር፡ በሩን አንኳኳ። በሩም በተከፈተ ጊዜ፡ እነዚያም ንስሐ የገቡ ነፍሳትን ሁሉ፡ እንዲህ አላቸው፦ "የሴቲቱ ዘር እኔ ነኝ። ሄኖክ ስለ እኔ ተናገረ እርሱ ነኝ... " በገነት ውስጥ፡ ሌላ ቦታ። አሁን፡ እነዚህ ሶስት ሰፍራዎችን በጭራሽ አትርሷቸው፥ የክፉዎች ሰፍራ፡ የጻድቃን ሰፍራ፡ እና ገሃነም ራሱ። አያችሁ?

415 ልክ እንደ ሰማያዊ ሦስትነት፡ እንደ፡ አባት፡ ልጅ እና መንፈስ ቅዱስ። እንደ አውሬው ሦስትነት፦ ሐሰተኛው ነቢይ፡ አውሬው፡ እና—እና የአውሬው ምልክት። ሁሉ እንዲያ ነው፡ አስታውሱ፡ ሁሉም ሥላሴነት ነው። ሥላሴነት በአንድ ይሰራልና፡ ፍጹምነት ያደርጋል። አንድ ፍጹም ነውና። የእናንተ ፍጽምናም፡ አንድ በሦስት ነው፦ ነፍስ፡ ሥጋ፡ እና መንፈስ፡ ውሃ፡ ደም እና ነርቮች። አያችሁ፡ ማንም ሁን፡ ፍጹም አንድ ትሆን ዘንድ ሦስት ነገሮች ያስፈልጉሃል። ባለ-ሶስት ማእዘን ብርጭቆ ወስደህ ፀሀይን በላዩ ላይ አሳልፍ፡ የተሰተካከለ ቀስተ ደመና ታገኛለህ። አያችሁ፡ ሁሉም ነገር፡ ፍጹም አንድ ለማግኘት ሦስት ነገሮች ይፈልጋል።

416 እና አሁን፡ እርሱ ሲሞት፡ መጀመሪያ ሄዶ፡ በእስር ቤት ላልነበሩት ነፍሳት እንደሰበከ አስታውሱ… ማለቴ በእስር ለነበሩት፡ “የሴትዋ ዘር” እሱ እንደሆነ መሰከትረላቸው። “ሄኖክ ከእልፍ አእላፍ ቅዱሳኑ ጋር ሲመጣ ያየው” እሱ እንደነበረ። በኖኅ እና በሄኖክ፡ እንዲሁም በቅዱሳን የተሰበከውን መጽሐፍ ቅዱስ፡ መሰከረላቸው፡ ይህም “እሱ እንደሆነ” ነው። ሁሉም ነገር እሱን ማወቅ ነበረበት!

417 ከዚያም ወደ ሲኦል ወረደ፡ የሞትና የሲኦልን መክፈቻ ከዲያብሎስ ተቀበለ።

418 ወደ ገነት ተመለሰና፡ አብራሃምን፡ ይስሐቅን፡ ያዕቆብንም፡ ጻዲቁንም አወጣ፡ ተነሥተውም፡ በማቴዎስ ወንጌል 27 ላይ፡ ከመቃብርም ወጥተው ወደ ከተማ ገቡ፡ እና በመንገድ ላይ ለሰዎች ታዩ። ሃሌ ሉያ! ይኸው!

419 አሁን፡ ስጋው ግን… ነፍሱ ለጠፉት እየመሰከረች እዚያ ሳለች፡ ቁልፎቹን ከዲያብሎስ ነጥቆ እየወሰደ በነበረ፡ እና እነ አብራሃም እና ይስሐቅ ይዞ እየተመለሰ ሳለ፥ ነፍሱ እዚህ ውስጥ ተኝታ ነበር… ነፍሱ በዚያ ወርዳ ትሰራ በነበረ ጊዜ፡ ስጋው ግን በመቃብ ተኝቶ ነበር። ኢየሱስ የተናገረው ለዚህ ነው… ሰዎች እንዲህ ይላሉ፡ “እሺ፡ ኢየሱስ ለምን እንዲህ አለ፡ ‘በሶስት ቀናት፡ እነሳዋለሁ፡ በሶስት ቀናት እነሳለሁ’? እሱ—አርብ ከሰአት በኋላ ሞተ፡ እሁድ ጠዋት ተነስቷልና።”

420 ግን ተመልከቱ፡ መዝገበ ቃላትን ብታገኙት “በሶስት ቀናት **ውስጥ**:” ነበር። ዳዊት በቅባት ስር ሆኖ፡ (በመንፈስ ቅዱስ ቅባት) ሥር ሆኖ ይህን አውቆ ነበርና፡ “ቅዱሴን መበስበስን እንዲያይ አልተወውምና፡” ብሏል። እርሱን የሚመለከት መሆኑን አውቋልና። ስለ እርሱ እንደነበረ አውቆ ነበር። እርሱ የእግዚአብሔር ቅዱስ ነበር፡ እና መበስበስ በሰባ-ሁለት ሰዓት ውስጥ እንደሚጀምር ያውቃል። በእነዚያ ሦስት ቀናት ውስጥ፡ እንደገና ከዚያ መውጣት ነበረበት፡ ምክንያቱም የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል አይወድቅም።

421 እና በዚያ ውስጥ ያለው እያንዳንዱ ቃል ኪዳን የእኔን እና የእናንተን ጉዳይ ይመለከታል፡ የእኛ ነው!

422 “ይህን አካል አፍርሱት፡ በሦስት ቀናት አነሣዋለሁ፡” አላቸው። “ነፍሴን በሲኦል ውስጥ አልተዋትም፡ ቅዱሴንም መበስበስን ያይ ዘንድ አልሰጠውም፡” ብሏልና።

423 በሦስት ቀናት ውስጥ ያንን ሥጋ ከዚያ እንደሚወጣ፡ አስቀድሞ ያውቃል። ሶስት ቀናት ሙሉ አልቆየም። አልቆየም፡ ወዳጄ፡ በጭራሽ አልቆየም። አርብ ከሰአት በኋላ እስከ እሑድ ጠዋት ድረስ ቆየ፡ የዚያ አካል አንድም ሕዋስ ሊበላሽ አልቻለም።

424 ሞተም፡ ሸቱም ተቀባ፡ በጨርቅ ተጠቅልሎ… ተኝቶም ነበር፡ በመቃብር ውስጥ ተቀምጦ ነበር። በዚያ ሞቃታማ፡ ረግረግ አገር፡ ከጥቂት ሰዓታት በኋላ ነገሮች ይበሰብሳሉና። ይኸውላችሁ-… ሞቃታማ በሆነ አካባቢ፡ ወደ መቃብር ስፍራ፡ ለመቅበር ስትወጡ፡ ሞቃት ስለሆነ፡ አፍንጫው፡ እና ሌሎች ነገሮች፡ ቶሎ ይበሰብሳሉ። የእሱም ሥጋ ስለነበረ፡ መበስበሱ አይቀርም ነበር። ነገር ግን አንድም ሕዋስ ከመበስበሱ በፊት፡ እግዚአብሔር፡ በነቢዩ በዳዊት በኩል እንዲህ እንደ ተናገረ ያውቃል፡ “ቅዱሴን መበስበስን ያይ ዘንድ አልተወውም።”

425 የእግዚአብሔርን ቃል ተቀብሎ እንዴት ኖረው! አሁን፡ እያንዳንዳቸው በዚያ ውስጥ ለእርሱ የተገቡትን ቃሎች፡ እግዚአብሔር እያንዳንዳቸውን ፈጸማቸው። አማኝን በሚመለከት ቃል ኪዳን ሁሉ፡ እግዚአብሔር የዚያን ተስፋ ሁሉ ይፈጽማል። አሜን። እውነት መሆኑን ብቻ እርግጠኛ ሁኑ። አሜን። ስለዚህ፡ ነፍሱ...

**እንዲህ ነው ብለህ ታሰባለህን...** ቆይ፡ ይቅርታ አርጉልኝ። **ሥጋው በመቃብር ውስጥ ባለበት በሦስቱ ቀናት ውስጥ የኢየሱስ መንፈስ የት ነበር?**

426 መንፈሱ በሲኦል ውስጥ ነበር፡ በታችኛው ክልሎች ውስጥ ነበር፥ እርሱም ተነሣ። እና ትንሽ ነገር ልጨምር—ሙሉ በሙሉ ሊረዳችሁ የሚችል ትንሽ አሳብ ልጨምርበት። በተነሣ ጊዜ፡ ከ... ከሙታን በተነሣ ጊዜ፡ የቤዛነት ሥራውን ገና ፈጽሞ አላጠናቀቀም ነበር። ትክክል ነው። ሁሉንም ነገር ማጽዳት ነበረበትና። ዋጋው ተከፍሎ ነበር፡ ቢሆንም የሲኦል ፍርሃት ግን፡ የመቃብር ፍርሃት ግን... እዚህ ጋር፡ እ—እሱ ሲሞት፡ በትክክል ቀጥሏል። ሲሞት ሥራውን አላቋረጠም፡ መሰበኩን ቀጠለ!... ? ... እንደሚመስለኝ፡ ልከኝነት የጎደለው ድርጊቴ ይቅር በሉኝ፡ ቢሆንም ግን አላቆመም!

427 በጭራሽ አትሞቱም! ሰውነታችሁ ለተወሰነ ጊዜ ሊያርፍ ይችላል፡ እግዚአብሔር ግን ያስነሳዋል፡ እንደሚያስነሣው ቃል ገብቷልና። እግዚአብሔር እንደማይጠፋ ሁሉ እናንተም አትጠፉም። እውነት ነው። ተመለከቱ፡ ከ—ከሞተ በኋላ፡ ለማን... ለደቀ መዛሙርቱ ሞተ። የሆነው፡ ተኝቶ ነው። ስለ አልዓዛር "ሂጄ እቀሰቅሰዋለሁ፡" ብሎ እንደተናገረ፥ አስተኙት። እግዚአብሔርም ሊቀሰቅሰው ተገባ።

428 ይኸውላችሁ፡ ወደ ታች ወረደ፡ መሰበኩንም ቀጠለ። እና እስር ቤት ለነበሩ ነፍሳት ሰበከላቸው። ወዲያውኑ ወደ ሲኦል ሄደ፡ ቁልፎችን ከዲያብሎስ ወሰደ። ተመልሶ መጣና በገነት ውስጥ ለነበሩት ሰበካቸው፡ እና በሦስተኛው ቀን እንደገና ተነሣ። ለአርባ ቀን ከሐዋርያቱ ጋር ተመላለሰ፡ በአርባኛው ቀንም፡ አረገ፥ ምክንያቱም፡ በእኛ ዘንድ የነበረውን ሁሉም ነገር፡ አጉል እምነቶች እና ሌሎች ነገሮች ሁሉ... አጉል እምነቶች ሁሉ፡ ጥርጣሬ ሁሉ አስወግዶ፡ በዕርገቱ ላይ ከምድር ወደ ክብር የጸሎት መሰመር አደረገ። ወጥቶም በግርማዊነቱ ቀኝ ተቀመጠ። ድል ነሺ! ፍጹም፡ ታላቁ ድል ነሺ ሆነ። ሞት ሊይዘው አልቻለም! ሲኦል ሊይዘው አልቻለም! ምድር እሱን መያዝ አልቻለችም!

429 እዚህ ምድር ላይ በነበረበት ጊዜ፡ የተሰጡት ነገር... ወደ ዝቅተኛው ከተማ እና ወደ ዝቅተኛው ሰዎች ወረደ፡ እና እጅግ የተዋረደ ስም ሰጡት። ይህን ያደረጉበት ሰዎች ናቸው። ወደ ዝቅጠኛይቱ ከተማ፡ ወደ ኢያሪኮ ወረደ። ትንሹ የተባለውን ሰው እሱን ለማየት ወደ ዛፍ ወጣ። ሰው እሱን ይሄን ያህል አሳነሰው። ሊሰጥ ከሚችለው በጣም የከፋ ሥራ፡ እግር-አጣቢ ድረስ ሆነ። ከሁሉም ዝቅ ያለ ሆነ። እናም ሊሰጡት ከሚችሉት ሁሉ የወረደ ስም፡ **ብዔል ዜቡል**፡ "የአጋንንት አለቃ" አሉት። ሰው ዝቅተኛውን ስም፡ ዝቅተኛውን ሰፍራ፡ ሰጠው እና ወደ ገሃነም ታችኛው ክፍል አወረደው።

430 እግዚአብሔር አስነሣው ወደ ሰማይም አወጣው፡ ከሰምም ሁሉ በላይ የሆነ ስም ሰጠው። ሃሌ ሉያ! ለምን፡ ሰማያትን ለማየት መፈተን ነበረበት።

ዙፋንህ ከሰማይ ሰማያት በላይ ከፍ ከፍ አለ። እናም በሰማይና በምድር የተሰየመው ታላቅ ሰም... ለእርሱ ሊሆን ተገባ። እግዚአብሔር ያደረገው ይህ ነው። ሰው ዝቅ አደረገው፡ እግዚአብሔርም ከፍ ከፍ አደረገው። ይኸው፡ ከታችኛው፡ እስከ ከፍተኛው።

431 ወደ ከፍተኛ ያወጣን ዘንድ እርሱ ዝቅተኛ ሆነ። እኛ በጸጋው፡ የእግዚአብሔር ልጆች እንሆን ዘንድ፡ እርሱ እኛን ሆነ። እሱ የወረደበት ቦታ ይህ ነውና። አሜን! ሰሙ ይባረክ። እኛም፡ አንድ ቀን የምንወጣበትን፡ መንገድ ሠራ፡ "እኔ ህያው ነኝና፡ ህያዋን ትሆናላችሁ።"

432 ኧረ፡ አይገርምም... ሰው ያንን ራዕይ ከያዘ፡ ሰው ሊያብራራለት የሚችልበት ጊዜ የለም። እንዲያውም ለማስረዳት ሞክረዋል፡ አእምሮአቸውን አጥተዋል፥ ይህ ታላቅ መዝሙር፥ "ኦህ፡ የእግዚአብሔር ፍቅር፡ እንዴት ድንቅ እና ንጹህ ነው! ምን ያህል ሰፊ እና ጠንካራ ነው!" የመጨረሻዋ ቁጥር... ወይም የመጀመሪያውን ቁጥር፡ ይመስለኛል፥ "ውቅያኖስ በቀለም ብንሞላው፡ ሰማያትም ብራና ቢሆን፥... " ያ የት እንደተገኘ ታውቃላችሁ? በእብዶች... በአእምሮ በሽተኞች ተቋም በግድግዳው ላይ ነው። የእግዚአብሔርን ፍቅር ማንም ሰው በፍጹም ሊያስረዳ አይችልም። ኧረ፡ እርሱ ለእኛ ያደረገው፡ ተነግሮ አያልቅም። እንዴ፡ በዚያ ውስጥ ምን አስተዋጽኦ መጨመር ትችላላችሁ? ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ፡ ጸጋው ነው። ጠፍቼ ነበር፡ ያልተገራ ሆኜ፡ አቅመ ቢስ ነበርኩ፡ ለምንም የማልጠቅም፡ ተራ ነበርኩ፡ እርሱ ራሱ በጸጋው መጥቶ አዳነን። ኦህ፡ ማይ። ጌታዬ... ይኸው ነው። ፍቅሩም ይህ ነው፡ በጎነቱ ይህ ነው።

433 አሁን ወደ ሰባት ደቂቃ እና ወደ አሰራ አምሰት ጥያቄዎች አሉብን...

## 62. ሴቶች ከቤተ ክርስቲያን ውጭ የግል ሥራ ቢሰሩ ትክክል ነው ብለው ታስባለህ?

434 አዎን። ይህ ጥያቄ ነው፡ መ... መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥያቄ አይደለም፡ ይሁን እንጂ... እንዲሁ እንደሆነ በትክክል፡ አሰባለሁ። አዎን፡ ወዳጄ፡ ሁላችንም አብረን ሠራተኞች ነን። ሴቶችም የራሳቸው ሰፍራ አላቸው፡ በርግጥም አላቸው። አዎን፡ ወዳጄ። ማድረግ የምትችሉትን የግል ሰራ ሁሉ ሰሩ፡ እግዚአብሔርም ይባርካችኋል።

እሺ፡ አሁን ደግሞ፦

## 63. እባክህን ሥላሴን በተመለከተ አብራራልን። ሁለቱ የተለያዩ ግለሰቦች ካልሆኑ በቀር፡ በአብ ፊት፡ ይማልድ ዘንድ... ልጅ በአባት ቀኝ እንዴት ይቆማል?

435 እሺ፡ ውድ ወዳጄ፡ ይህ ጉዳይ... ይሄንን—የመገለጥ ጉዳይ ነው። ኢየሱስ "እኔና አብ አንድ ነን፡" ካለ፡ ታዲያ እንዴት ሁለት ይሆናሉ? አየህ? ሰለዚህ፡ ሁለት አይደሉም።

436 አንዲት ሴት በአንድ ወቅት እንዲህ አለችኝ፡ ያንን እዚህ ተናግሬዋለሁ፡ እና "አንተና ሚሰትህ—ሁለት ብትሆኑም፡ አንድ ናችሁ፡" አለችኝ።

437 እኔም "ሰለ እግዚአብሔር እና ልጅ ግን፡ ከዚህ በተለየ መልኩ ነው፡ አየሽ፡" አልኳት። "እኔን ታይኛለሽን፡" አልኳት?

"አዎን።"

“ሚስቴንስ ታያታለሽን? ”

“አትታየኝም።”

438 እኔም አልኳት፡ “እንግዲያውስ፡ የአባት እና የልጅ ይለያል፥ ኢየሱስ ያለው፡ ‘እኔን ያየ፡ አብን እየ ነው።’” አየሽ?

439 አባት እና ልጅ... አባት ሁሉን ቻይ የሆነው ያሕዌ እርሱም (አምላክ) የተቀባ የእግዚአብሔር ልጅ በሆነው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በሚባል ማደሪያ ውስጥ ያደረ አምላክ ነው። ኢየሱስ ሰው ነበር፡ እግዚአብሔር መንፈስ ነው። እግዚአብሔርንም መቼም ቢሆን ከቶ ያየው የለም፡ ነገር ግን የአብ አንዲያ ልጅ ተረከው። እ... እ... ማንነቱ፡ ሰብእናው፡ አምላክነቱ፡ በሱ የነበረው ነገር ሁሉ፡ አምላክ ነበረ! እርሱ ከእግዚአብሔር ያነሰ ወይም የበለጠ ምንም አልነበረውም። በዚህ ሁሉ ግን፡ ሰው ነበረ። እርሱ ሰው ነበር፡ እግዚአብሔር ያደረበት ቤት። ልክ ነው፡ እርሱ የእግዚአብሔር ማደሪያ ነበር።

440 አሁን፡ በዚህ ላይ አንዳንድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል ከፈለጋችሁ፡ ወንድም ኔቪል፡ ቅዱስ ማርቆስ 14፡62 ብታገኛልኝ። እና እህት ዉድ፡ ኤፌሶን 1፡ 20 ክፈቺልኝ። መጽሐፍ ቅዱስ የያዘ ሌላ ሰው አለ? እሺ፡ እጃችሁን ከፍ አርጉ። እህት አርኖልድ፡ አንድ ይዘሻል? እሺ፡ አንጽቺም የሐዋርያት ሥራ 7፡55 ያዢልኝ። እሺ። ማርቆስ 14:62፡ ወንድም ኔቪል፡ እና እህት ዉድ ኤፌሶን 1:20፡ የሐዋርያት ሥራ 7፡55፡ እህት አርኖልድ።

441 እሺ፡ አገኘኸው፡ ወንድም ኔቪል? እሺ፡ አሁን አንብብልን። [ወንድም ኔቪል መጽሐፍ ቅዱስ አነበበ—አርታዒ።]

**[ኢየሱስም፡ እኔ ነኝ፥ የሰው ልጅም በኃይል ቀኝ ሲቀመጥ፡ በሰማይም ደመና ሲመጣ ታያላችሁ አለ።]**

442 እሺ፡ አሁን፡ ኢየሱስ የተናገረውን፡ የመጀመሪያውን ሐረግ አስተውሉት፡ “**እኔ ነኝ**።”

443 “**እኔ ነኝ**።” ያ **እኔ ነኝ** ማን ነበረ? በዓለም ላይ ሁሉ ላይ ይህን ሊተረጉመው የሚችል ሰው አልተገኘም። እናንተ መዝገበ-ቃላትን እና የመሳሰሉትን የምታነቡ... ብትሆኑም፡ J-v-h-u... የሚያውቀው ሰው አልተገኘም። የዕብራውያን ሊቃውንት እንኳን በፍጹም ሊያደምጡት አይችሉም። በዚያ በሚቃጠል ቁጥቋጦ፡ በዚያ ቀን ከሙሴ ጋር በተገናኘ ጊዜ፡ J-v-h-u ነበር። ስለዚህ ሲያደምጡት እንደዚህ ነው “J-o-h፡ ጄሆቫ፡” ይሁን እንጂ “ጀሆቫ” አይደለም። J-v-h-u ነው፡ እያችሁ፡ ማንም አያውቀውም።

444 እናንተም “እንግዲህ፡ ለሙሴም ይህን ማድረግ አልቻለውም፡” ትላላችሁ።

445 እርሱም “እኔ ማን ልበል፡” አለ?

446 እንዲህም አለ፡ “እንዲህ በል፡ ‘**እኔ ነኝ**’ ልኬሃለሁ። **እኔ ነኝ**።”

447 አሁን አስተውሉ፡ **እኔ ነኝ** አሁናዊ ጊዜ ነው፡ “እኔ ነበርኩ” ወይም “እኔ እኖራለሁ” ሳይሆን፡ **እኔ ነኝ**። አሁን፡ እንዲህ አለ፡ “ይህም ለትውልድ ሁሉ መታሰቢያ ይሆናል፡ **እኔ ነኝ**።”

448 አሁንም እዚህ ጋር ኢየሱስ በዚያ በበዓሉ ቀን ላይ ቆሞ ተመልከቱት። እንዲህም አሉት፡ “እብድ እንደሆንክ አሁን አወቅን።” በግልጽ ቃላት፡ “አንተ እብድ ነህ።” (**እብድ** ማለት “ቀውስ።”) “ቀውስ እንደሆንክ እናውቃለን። ሳምራዊ ነህ፡ አጋንንት አለብህ።” (ቅዱስ ዮሐንስ፡ ምዕራፍ 6 ላይ) እርሱም፡ “አሁን፡ አንተስ ሃምሣ አመት በላይ... ሳትሆን፡ አብርሃምን አይቻለሁ ትላለህን? ” (ዕድሜው ትንሽ ያረጀ መስሎ ሊታይ ይችላል፡ እሱ ግን ሠላሳ ብቻ ነበር፡ ሥራው ነው እንጂ።) አሉትም፡ “አንተ ከሃምሣ አመት በላይ ሳትሆን፡ ‘አብራሃምን አይቻለሁ’ ትላላአህን? ቀውስ መሆንህን አሁን አወቅን።” አያችሁ?

“አብርሃም ከመወለዱ በፊት፡ **እኔ ነኝ**፡” አላቸው።

449 ይህ “**እኔ ነኝ**፡” እርሱ ታላቁ **እኔ ነኝ** ነበረ። እነሆ ለእነዚህ አይሁዶች እንደገና ተናገራቸው፡ አያችሁ፡ “**እኔ ነኝ**! በኃይልም ቀኝ ሰመጣ ታዩኛላችሁ ያን ጊዜ... ” ልክ ነው?

450 እንደገና እንብብልን፡ ወንድሜ። [ወንድም ኔቪል መጽሐፍ ቅዱስ አነበበ—አርታዒ።]

> [... **የሰው ልጅም በኃይል ቀኝ ሲቀመጥ፡ በሰማይም ደመና ሲመጣ ታያላችሁ።**]

451 እህት ውድ፡ አሁን አንቢቢልን። [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ። ሲስተር ዉድ፡ “ኤፌሶን 1:20” ነው ብላ ጠየቀች?—አርታዒ።] አዎን፡ እመቤት። [እህት ዉድ መጽሐፍ ቅዱስ አነበበች።]

> [**ክርስቶስንም፡ ከሙታን ሲያስነሣው፡ በሰማያዊ ስፍራ በቀኙ አስቀመርጠው።**]

452 እሺ፡ የአንቺም አንብቢ፡ እህቴ። አያችሁ፡ ተመሳሳይ ነው። [እህት አርኖልድ የሐዋርያት ሥራ 7:55ን አነበበች—አርታዒ።]

> [**እርሱ ግን፡ መንፈስ ቅዱስንም ተሞልቶ፡ ወደ ሰማይ ትኵር ብሎ ሲመለከት፡ የእግዚአብሔርን ክብር፡ ኢየሱስንም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አየ፡**]

453 አሁን፡ ተመልከቱ፡ እ-... እግዚአብሔር ትልቅ ቀኝ እጅ ኖርት፡ አያችሁ፡ ኢየሱስም በቀኝ እጁ **ላይ** ተቀምጦ ነበር ማለት አይሆንም። **ቀኝ እጅ** ማለት “ስልጣን” ማለት ነው። አያችሁ? ለምሣሌ፡ እኔ የአንዲት ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ፡ ወይም የሆነ ነገር ቢሾፕ ብሆን፡ እና ወንድም ኔቪል የእኔን ስፍራ ቢይዝ፡ እሱ ቀኝ እጄ ይሆናል። አያችሁ፡ ያ ማለት እርሱ... ቀኝ እጄ ይሆናል ማለት ነው።

454 አሁንም፡ ኢየሱስ በስልጣኑ ቀኝ ይገኛል። እዚህ በኤፌሶን ላይ፡ እንደተናገረው፡ ሲያብራራው፡ በስልጣኑ ቀኝ እንደሚገኝ፡ ተናግሯል። “በሰማይና በምድር ያሉ ስልጣናት ሁሉ” (ከትንሣኤው በኋላ፡ ሲናገር) “ለእኔ ተሰጥቶኛል አለ። በሰማያት እና በምድር ሁሉ ስልጣን ተሰጠኝ። እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ፡ በአባት፡ በልጅ፡ በመንፈስ ቅዱስ ሰም እያጠመቃችኋቸው፡ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ አስተምሯቸው፥ እነሆ፡ እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ፡ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።”

455 “በሰማይና በምድር ስልጣን ሁሉ።” የት ነው... ከሱ በቀር ሌላ አምላክ እዚያ ያለ ከሆነ፡ አቅመ ቢስ ነው። አያችሁ፡ ሌላ አምላክ ሊኖር አይችልም። “የሰማይ እና የምድር ስልጣን ሁሉ” በእጄ ውስጥ ነው። ስለዚህ፡ አያችሁ፡ “በቀኝ ቆሟል፡” (ሰውዬው እንደጠየቀው ጥያቄ)፡ ይህ ማለት እንዲህ አይደለም...

456 አሁን ተከታተሉኝ፡ አካሉ... እግዚአብሔር መንፈስ ነው። አዎ፡ ስንቶቻችሁ ትረዱታላችሁ? “ኣሜን፡” በሉ። እግዚአብሔር መንፈስ ነው፡ ኢየሱስ ሰው ነው፡ ኢየሱስም ሥጋ ሆነ። ኢየሱስ... እግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነ፡ አያችሁ፡ እሱን ማየት ከቶ አይቻለንም። መንፈስን ማየት አትችሉምና። “መቼም እግዚአብሔርን ያየው ማንም የለምና።” ማንም ሰው እግዚአብሔርን ማየት አይችልም።

457 ስለዚህ እንዲህ ልበላችሁ፡ “እኔን በፍጹም አይታችሁኝ አታውቁም።” በህይወታችሁ ዘመን ሁሉ እኔን አይታችሁኝ አታውቁም፡ ወደፊትም አታዩኝም። ይህ እውነት ነው። ይህን ሰው የሚተርከውን አካል፡ ይሄኛውን ታያላችሁ እንጂ። አሁን፡ ይህ አካል የዘላለም ሕይወት የለውም፡ መንፈስ ግን የዘላለም ሕይወት አለው። ይህ አካል ይሞታል፡ ነገር ግን እንደ ስንዴ ቅንጣት ወደ መሬት እንደምትገባ፡ በምሳሌው እንደገና ይወጣል። ክርስትና የተመሰረተው በትንሣኤ መሰረት ላይ እንጂ፡ በመተካት መሰረት ላይ አይደለም። ትንሳኤ፥ ያው ኢየሱስ ወረደ፡ ያው ኢየሱስ ተመልሶ መጣ። ባለ ቀይ-ጸጉር ሆናችሁ ከሞታችሁ፡ ባለ ቀይ-ጸጉር ሆናችሁ ትመለሣላችሁ። ባለ ጥቁር-ጸጉር ሆናችሁ ከሞታችሁ፡ ባለ ጥቁር-ጸጉር ሆናችሁ ትመለሣላችሁ። አያችሁ፡ ትንሳኤ ነው።

458 ምግብ ስትመገቡ... በቅርብ ጊዜ፡ አንድ ዶክተርን ጠየቅኩት፡ እንዲህ በማለት፡ “የአስራ ስድስት አመት ልጅ ሳለሁ... በበላሁ ቁጥር፡ ሕይወቴን ይታደስ ነበር ለምንድነው? ”

459 “ትክክል ነው፡” አለ።

460 አዎን ይ—ይህ ስጋ እንዲህ ይሰራል... በየጊዜው አ—አዲስ ሕዋስ ይሰራል... ማለቴ ምግቡ የደም ህዋሳት ይሰራል፡ እና ያ የደም ሕዋስምየበለጠ ጠንካራ እንድትሆን ያደርጋል። የምትኖሩት እንደዚያ ነው። ስለዚህ፡ እናንተ በህይወት እንድትኖሩ፡ ሁሌም አንድ ነገር መሞት ይኖርበታል። በየቀኑ፡ አንድ ነገር ይሞታል፥ ስጋ ከበላችሁ፡ ላሟ ትሞታለች፥ ወይም የምትበሉት ሁሉ ይሞታል፡ ዓሣውም ይሞታል፥ ወይም ዳቦውን ለመሰራት፡ ስ—ስንዴው ይሞታል፥ ድንች ወጥ ለመሰራት፡ ድንች ትሞታለች፥ እና እ... እያንዳንዱ ዓይነት ሕይወት፥ በሙት ነገር ብቻ ነው መኖር የሚችለው።

461 እናንተም አንዳች ነገር ስለሞተላችሁ ለዘለአለም በህይወት ትኖራላችሁ፡ እርሱም ኢየሱስ ነው። ቤተ ክርስቲያን አባል ስለሆናችሁ አይደለም፡ ስለተጠመቃችሁም አይደለም፡ ክርስቲያን ነን ስላላችሁም አይደለም፥ የፈሰሰውን የኢየሱስ ክርስቶስን ሕይወት ስለተቀበላልችሁ ነው... ስለ እናንተ የፈሰሰው ደም፡ እንደ ግል አዳኛችሁ ስለተቀበላችሁት ነው።

462 አሁን፡ አስተውሉ፡ እንዲህ ልጠይቅ። እንዲህ **ልጠይቃችሁ** እፈልጋለሁ። ይህን ተመልከቱት፡ በጣም ደስ ይላል። ምናልባት ከዚህ በፊት እዚህ ተናግሬው

ሊሆን ይችላል (አላውቅም)፥ በየቦታው በመሰበክ ምክንያት፡ በሌላኛው ላይ የተናገርከውን ይረሳልና... የተወሰኑ ቦታዎች። ታዲያ፡ ግን፡ ለምንድነው...

463 አሁን፡ እህት ስሚዝ፡ ትመስለኛለች... ወንድም ፍሌማንን ያን ጊዜ ልወቀው አልወቀው እንጃ። እና ትሪፊናን፡ ትንሽ ልጅ እያለች አስታውሳታለሁ። ያን ጊዜ ታስታውሳላችሁ፡ አንዳንድ ነገሮች እሞካክር ነበር... ትንሽ፡ ወፈር ብዬ፡ አጠር ያልኩ፥ የሚወዛወዝ፡ ጥቁር ጸጉር ያለው ነበርኩ። ቦክስ ተፋላሚ ነበርኩ። ኦህ፡ በአለም ላይ እኔ ቄንጠኛ ሰው ነኝ ብዬ አስብ ነበር። “ኦህ፡” እንዲህ ብዬ አስብ ነበር፡ “እኔን ማንም አይችለኝም። በጭራሽ፡ ወዳጄ።” ይሁን እንጂ በዚያ ነገር ተ—ተታለልኩ፡ አያችሁ። እኔ ግን... አሁን፡ ሳሰበው፡ “ኦህ፡ ማይ።” “ይህን ነገር ጀርባዬ ላይ ብትጭኑብኝ፡ ተሸክሜው ጎዳናው ላይ መዞር እችላለሁ፡” ብዬ አስብ ነበር። አዎን፡ ምንም አይበግረኝም። እና ምግብ በተመገብኩ ቁጥር፡ በየጊዜው እያደግኩ እና እየጠነከርኩ እቀጥል ነበር። በየጊዜው አዲስ ህይወት እጨምር ነበር... ልክ እንደዛሬው ጎመን፡ ድንች፡ ባቄላ፡ እንዲሁም ስጋ፡እመገብ ነበር። በየጊዜውም እየጠነከርኩ እያደግኩ ነበር። እና ወደ ሃያ-አምስት ገደማ ስደርስ...

464 ሁላችሁም ታውቁኛላችሁ፡ ያኔ ከምበላው ምግብ ይልቅ አሁን የምመገበው፡ እጅግ የበለጠ ነው። የተሻለውን እየበላሁ ነው፡ ሁላችንም እንዲሁ ነን። ለምንድነው፡ ወንድም ኢገን፡ ታዲያ፡ አሁንም የተሻለ ምግብ እየበላሁ ከሆነ፡ የበለጠ፡ የተሻሉ ቪታሚኖች እና ሁሉም ነገር... እና ብዙ ባበላሁ ቁጥር፡ ቀስ በቀስ እየወረድኩ ሄድኩ። እነሆ አሁንም የጎበጠ-ሽማግሌ፡ ራስ በራ፡ እና ሽበታም፡ የተሸበሸቡ እጆች ያሉት፡ ፊቱ የተጨማደደ፡ ትከሻዎቹ የረገቡ፡ ማለዳ ለመነሣት ደካማ ሰው ሆኛለሁ፡ እና... ኦህ፡ ማይ። ለምንድነው? በበላሁ ቁጥር ህይወቴን ካደሰኩት፡ ለምንድነው?

465 ከአንድ ማሰሮ ውስጥ ውሃ ወደ ብርጭቆ ውስጥ ከቀዳሁ፡ እና ግማሽ የሚሆን ከሆነ፡ ወደ ላይ ከሞምላት ይልቅ ቁልቁል የሚወርድ ከሆነ፥ በሞላሁት ቁጥር፡ በፍጥነት ይወርዳል። ይኸውላችሁ። አረጋግጥልኝ ብትባሉም በሳይንስ ይሄን ማብራራት አይቻላችሁም። እግዚአብሔር የቀጠረው ነገር መሆኑን የሚያረጋግጥልን ይህ መጽሐፍ ብቻ ነው፥ ቀጠሮ ነው፡ እግዚአብሔር ጉዞ ላይ ሆነን አይቶናል።

466 እናንተ ሽማግሌዎች ወንዶች፡ እና እናንተ አሮጊቶች ሴቶች ሆይ፡ ምናልባት አንዳንዶቻችሁ—ባላችሁ ወይም ሚስታችሁ የሞቱባችሁ ሆይ፡ ይህ ምንም—ምንም ሊያስጨንቃችሁ አይገባም። ሃሌሉያ! ከአድማስ ባሻገር፡ በሙላት፡ እየተጠባበቁ፡ ከእናንተ ጋር ለመሆን እየናፈቁ ይገኛሉ። ልክ ነው፡ በእርግጠኛነት፡ እንዲሁ ናቸው። እንደገና አብረው ለመሆን እየናፈቁ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እነርሱ፡ ከመሠዊያው በታች የሚያለቅሱ ነፍሳት እነርሱ ናቸው ይላል፡ “ጌታ ሆይ፡ እስከ መቼ? ” አያችሁ? በትክክለኛው ሁኔታቸው ላይ አይደሉም።

467 እግዚአብሔር መላእክትን ፈጽሞ አላደረገንም፡ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠረን። የእግዚአብሔር የማሰብ ችሎታ ውጤት፡ ስለሆንን—ሁሌም ወንድ እና ሴት መሆናችን አይቀርም። ሁሌም ወንድ እና ሴት መሆን እንችላለን።

468 ግን ይሄን እንዴት ይሆናል? እያችሁ፡ አንተና ፍቅረኛህ፡ ወደ መሰውያው የመጣችሁ ጊዜ ምናልባት እንዲህ ታስቡ ይሆናል፡ በዚህ በተቀደሰ ጋብቻ ሁለታችንም ሕጋዊ ባለትዳሮች ሆነን አብረን እንኖራለን፡ በምስክርነታችሁ ሁሉ፡ እና በእግዚአብሔር ጸጋ፡ እንዲሁም በምትገቡት ቃል ኪዳን ወዘተረፈ ትጋባላችሁ። እንደምታውቁት፡ ከሁሉ በፊት ሁለታችሁ፡ አንድ ነገር ታስተውላላችሁ። እርሱ ቀድሞ ባለ ወርቃማ ጸጉር፡ ቀና ያለ ነበረ፥ ማማም ውብ የሆነች፡ ባለ ቡኒ ዓይን፡ ወይም ባለ ሰማያዊ ዓይን፡ ወይም ሌላ የምታምር ነበረች። አቤት፡ እንዴት እንደምታያት። ወጥተሽ፡ አባባን ስታዪው፡ "አሁን፡ ትከሻው ወደ ኋላ ቀጥ ብሏል"፥ ከጥቂት ጊዜ በኋላ መውደቅ ይጀምራሉ። እማማ ሽበታም-ጸጉር፡ አርትራይተስ ይመጣባታል ወዘተ። እና ከጥቂት ጊዜ በኋላ፡ ትሞታለች፡ ወይም ይሞታል።

469 ይህ ምን ነበር? እግዚአብሔር በዚያ ቆማችሁ ባያችሁ ጊዜ፡ እንዲህ ይላል፡ "ይኸው፡ እኔ የምፈልግህ በዚህ መንገድ ነው። በጣም ጥሩ። ሞት ሆይ፡ ናና ግባበት፡ እስክፈቅድልህ ድረስ ግን እንዳትወስደው።"

470 ኦህ፡ ኦህ፡ ኢዮብን አሰብኩት። አዎን፡ እግዚአብሔር ወደ ታች እያየው ነበር፡ ኢዮብም እግዚአብሔር እንደሚወደው ያውቃል። (እና ሊወስዳችሁ እንደማይችለው ልብ በሉ።) እንዲህ አለው፡ "በእጅህ ውስጥ አስገባው፡ ህይወቱን ግን እንዳታጠፋ።"

471 እና ከሁሉ በፊት የምታስተውሉት፡ ትከሻዎች መጉበጥ ይጀምራሉ፡ እና ከጥቂት ጊዜ በኋላ ትሞታላችሁ። ምን ተፈጠረ?

472 አሁን፡ በትንሣኤ ሞትን የሚያመላክት አንድ ነገር አይኖርም። ይህችን ምድር የሚያመላክት አንድ ነገር ሊኖር አይችልም፡ እ... እያችሁ፡ በእግዚአብሔር ፈቃድ መጣችሁ፡ ሕይወትም አገኛችሁ። በኋላ ሞት ገባና፡ ይዟችሁ ወረደ። አንድ አይነት ምግብ እና ሁሉንም ነገር ትበላላችሁ፡ በሁሉም፡ አንድ አይነት የሆነ ውሃ ትጠጣላችሁ፡ ሞት ግን ይገባል። ምስሉ አስቀድሞ የተዘጋጀ ነው። ሃሌሉያ! በትንሣኤ እንደገና ህያው ትሆናላችሁ። እና ሞት የለም፡ ወይም ሞት መሳይ፡ ወይም እርጅና፡ ወይም አንካሳ ወይም ማንኛውም ነገር አይኖርም። የማይሞቱ ሆነን፡ በእርሱ አምሳል፡ ለዘላለም ፍፁማን እንሆናለን። ሃሌ ሉያ። ኦህ፡ እ... ይሄ ነገር ሁሉንም ዕልል ያሰብላል፡ በተለይ በእኔ ዕድሜ ላለ ሰው።

473 እንደምገምተው፡ ከመቼም ጊዜ በላይ፡ ይህን የምታስቡት፡ በእኔ ዕድሜ፡ ይመስለኛል። እያችሁ፡ እናንተም ወደዚያ ወደመለወጥ ሂደት ውስጥ ትገኛላችሁ። መ... መደነቅ ትጀምራላችሁ፡ "ይህን ሁሉ ምንድነው? ምን ሰራሁ? " ወደ ኋላ መለስ ብዬ፡ ሳስበው፡ "ወይኔ፡ ጉዴ! አቤት፡ ይህ ሁሉ የት ገባ፡ ጌታ ሆይ? እነሆ እኔ፡ አርባ-ሰምንት ዓመቴ ሆኛለሁ፡ ከሁለት ዓመታት በኋላ፡ የመቶ ግማሽ እሆናለሁ። አቤት! እንጃ ብቻ... ወደ ጌታ ያመጣኋቸው ጥቂት ነፍሳት ጥቂት ናቸው፥ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ እና ሌሎች ሚሊዮኖችን ማሸነፍ እፈልጋለሁ።" አምላክ ሆይ፡ እርዳኝ።

474 ለእረፍት ወደ ቤት መምጣቴ እንኳን በራሴ ያሳፍረኛል። አስበዋለሁ፡ "ኦህ፡ መከሩ ደርቋል፡ እና ሠራተኞች ጥቂቶች ናቸው። በየቀኑ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ በኃጢአት እና በኀፍረት እየሞቱ ነው፡ ጩኸታቸውን ይሰማል።" በመሸ ቁጥር ለመተኛት ወደዚያ ስሄድ በምድሪቱ የሚኖሩ አረማውያን ሲጮኹ

እሰማቸዋለሁ። ከኋላዬ እየተጓተቱ፡ በሺህዎች እንዴት እንደሚመጡ፡ እና—እና ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ታሪኩን ለመስማት ብቻ እዚያው አውሮፕላን ማረፊያው ላይ ጥሰው እንዳይገቡ ለመከልከል፡ ሚሊሻዎች እንዲመጡ ማድረግ ግድ ነው።

475 እዚህ ግን ለምንን፡ በጋዜጣዎች እና በሌላ መንገዶች ማስታወቂያ ሰርተን፡ የሚቀመጡባቸውን ቅንጡ ሰፍራዎች፡ ድንቅ ዝማሬዎች አዘጋጅተን ስንጠራቸው፡ ይመጡና እንዲህ ይላሉ፡ "**እይይይ**! በርግጥ፡ ደህና ቢሆንም፡ የእኔ እምነት አይደሉም።"

476 ኦህ፡ ማይ፡ ይህ ለ—ለ—ለስንት ጊዜ እንዲህ ሆኖ ይኖራል? ይህ ል—ልክ አይደለም። እና እዚያ ያሉ ሰዎች በደስታ ሊቀበሉት የሚችሉትን በመቶ ቢሊዮን ቶን የሚቆጠር ምግብ፡ ወደ ቆሻሻ መጣያ ውስጥ እንጥላለን። እነርሱም እንደ እኛ አንድ አይነት የምድር ፍጥረት ናቸው። ማይ፡ እ… እንግዲህ፡ እንደዚህ ሆኖ አይቀጥልም።

477 እሺ፡ አሁን፡ አባት ማን ነው? አባትና ልጅ አንድ ናቸው። በአንደኛ ዮሐንስ 5፡7 ላይ፡ ተመልከቱ፡ እንዲህ ይላል፡ "በሰማይ የሚመሰክሩ ሦስት ናቸውና፡ አባት፡ ቃል (ማለት ልጅ)… አባት፡ ልጅ፡ እና መንፈስ ቅዱስ፥ እነዚህ ሦስቱ አንድ ናቸው።"

478 "በምድር ላይ የሚመሰክሩት ሦስት ናቸው፡ እነርሱም ውሃ፡ ደም፡ እና መንፈስ ናቸው።" ከክርስቶስ አካል የወጡ ሦስቱ ንጥረ ነገሮች እነዚህ ናቸው። ጎኑን ወጉት፥ ውሃ ወጣ፡ ደምም ወጣ፡ "መንፈሴን በእጅህ አደራ ስጠሁ አለ።" እያችሁ፡ ሦስቱ ንጥረ ነገሮች እነዚህ ናቸው። እነዚህ ሦስቱ አንድ አይደሉም፡ ነገር ግን በአንድ **ይስማማሉ**።

479 አባት፡ ልጅ፡ መንፈስ ቅዱስ፥ አንደኛ ዮሐንስ 5፡7 ላይ፡ እንዲህ ይላል፡ "እነዚህ ሦስቱ አንድ **ናቸው**።"

480 "ውሃ፡ ደም፡ እና መንፈስ በአንድ **ይስማማሉ**።" አንድ አይደሉም፡ ነገር ግን በአንድ **ይስማማሉ**። ስለዚህ አባት… እና አካል ማድረግ የሚችለው ብቸኛው ነገር፡ ይህ አካል በሚደርስበት ቅጣት፡ እግዚአብሔር ራሱን ባየ ቁጥር፡ መገናኛው በዚያ ነው… እያችሁ፡ እዚያ ይገናኛል። በእርሱ እና በፍርዱ መካከል ደሙ ሲቆም የሚያየው በዚያ ነው። እነሆ ቃሉ፡ እንዲህ ተብሎ ነበር፡ "ከእርሱ በበላህ ቀን፡ ያን ቀን ሞትን ትሞታለህ።" እዚህ ጋር ግን ኢየሱስ እንዲህ አለ፡ "በ… ፋንታቸው እኔ እሞታለሁ። ይኸው፡ በፋንታቸው እኔ ልሙት።"

481 በቀደም ታሪኬን በዚያ ቤት ውስጥ የነበረችው ሴትዮ እጅግ አስቀያሚ ነገር የነበረች ትዝ ትላችኋለች? እኔም የፈረድኩባት፡ እንዲህ በማለት፡ "አምላክ ሆይ፡ ምነው ይህ ሰፍራ ባፈነዳኸው? " ከዚያም እንዲህ **አሳየኝ**፡ እያችሁ። እና ወደ እሷ ሄጄ የሆነውን ነገር ነገርኳት።

አሁን፡ ይህ የመጨረሻ ጥያቄዬ ነው።

## 64. በመጽሐፍ መሰረት፡ አይሁዶች፡ ከንጥቀት በፊት… ቤተክርስቲያን ከመነጠቋ በፊት ክርስቶስን የሚቀበሉ ይመስልሃልን?

482 ይኸውላችሁ፡ ይህ የግሌ ሐሳብ ነው… የቤተክርስቲያንን መነጠቅ በእውነት እ—እ—እምናለሁ። እና ጊዜ ቢኖረን፡ እናየው ነበር፡ እ—

አሁን ግን ዘጠኛ ሰዓት አልፏል። ይኸውላችሁ፡ አይሁዶች ክርስቶስን በዳግም ምጽአቱ እንደሚቀበሉ አምናለሁ። አሁን አስታውሱ፡ ሰውየው ይህንን እንዲረዳ፡ ዓይኖቻችን ታውረናል፡ ማለቴ፡ እኛ ማየት እንችል ዘንድ አይኖቻቸው ታወሩ። በዚህ ጉዳይ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገር፡ ማንም ያውቃል። ልክ ነው? ጳውሎስ እንደተናገረን... አይኖቻችን... ማለት እኛ ክርስቶስን መቀበል እንድንችል አይሁዶች መታወራቸውን ተናግሯል። አያችሁ? ስለዚህ እኛ በጉዲፈቻ የዱር የወይራ ዛፍ ከመሆን ወደዛፉ የገባን ነን።

483 አሁን የእኔ አስተያየት ይኸውና፡ ልንገራችሁ... እንዲህ ጠይቀውኛልና፡ “እንዲህ ታስባለህን ብለውኛል... ? ” አሁን ይከናወናል ብዬ የማስበው መንገድ ይህ ነው። እኔ አላውቀውም። መቼም ቢሆን፡ በእግዚአብሔር ቸርነት እና ምህረቱ፡ እዚያ እንደምንደርስ እርግጠኛ ነኝ፥ አያችሁ፡ በጸጋው፡ ምንም ቢሆን። ማወቅ አልችል ይሆናል፡ እኔ የማስበው ግን እንዲህ ይኸው ነው። በመጨረሻው ሰዓት ላይ እንደሆንን አምናለሁ። የአህዛብ ዘመን አሁን እያበቃ ነው ብዬ አምናለሁ። በደጅ ላይ ነን ብዬ አምናለሁ።

484 እና አሁን አይሁዶችም፥ አይሁዶች የሚሳሳቱት ሁለት ነገሮች እነዚህ ናቸው፥ ሊያዩት አይችሉም፥ በአሕዛብ ምክንያት፡ ለአንድ ነገር፡ ታውረዋል፡ ብዙውን ጊዜ...

485 በቤንተን ሃርበር ከአንድ አይሁዳዊ ጋር ተነጋግሬ ነበር፡ እህት ስሚዝ፡ እና ሌሎቻችሁ ምን እንዳለኛ ታውቃላችሁ? እስራኤላውያን በሚኖሩበት አካባቢ... በእስራኤላውያን መኖሪያ ነው። ጥያቄው ስለ ዓይነ ስውር ሰው መፈወስ ነበረ። እርሱም፡ “አይሁዶችን... እግዚአብሔርን በሦስት ቁርጥራጮች ቆርጣችሁ ለአይሁዳዊ መስጠት አትችሉም፥ አባት፡ ልጅ፡ መንፈስ ቅዱስ ማድረግ አይቻላችሁም።” “አይሁዳውያን ጣዖት አምላኪዎች አይደለንምና፡ እኛን ማሳመን አትችሉም፡” አለኝ። “**አንድ** አምላክ እናምናለን፡” አለኝ። አያችሁ?

486 እግዚአብሔር አባት፡ እግዚአብሔር ልጅ፡ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን እያላችሁ፥ እግዚአብሔርንም ሦስት ለማድረግ ትፈልጋላችሁ፥ አይሁዳዊን በግልጽ እንደማሳወር ነው፡ የተሻለ ነገር ያውቃል። ከዚያ የተሻለ ነገር ያውቃልና። ሶስት አማልክት አሏችሁና፡ ይህ እንደ ጣዖት አምልኮ፡ ጣዖት አምላኪ ያደርጋችኋል። አንድ ራሱ ያው አምላክ ልታደርጓቸው ይገባል፡ ሦስት አማልክት ሳይሆን፡ የአንድ አምላክ ሦስት መገለጫዎች ናቸው። አያችሁ፡ እግዚአብሔር በአባትነት አገለገለ፡ በልጅነቱ አገለገለ፡ አሁን ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ ዘመን እያገለገለ ይገኛል። ያው አንዱ-አምላክ ነው።

487 በአባት፡ በልጅ፡ በመንፈስ ቅዱስ ስም እንድናጠምቅ የተሰጠን ትእዛዝ ለዚህ ነው፥ ምክንያቱም፡ ሰሞች... በሰሞች ሳይሆን፡ **ስም**፥ ሰሞች አይደለም፡ ወይም በአብ ስም፡ በልጅ ስም፡ በመንፈስ ቅዱስ ስም ሳይሆን፥ “በአባት፡ በልጅ፡ በመንፈስ ቅዱስ ስም።” አያችሁ፡ ይህ አንድ አምላክ ክርስቶስ መሆኑን እወቁት። አያችሁ፡ እርሱ ነው፡ ሌላ መንገድ ሊኖር አይችልም። አያችሁ? መጽሐፍ ቅዱስም...

488 ሰ—ስለዚህ የእኛ መገለጥ ስህተት ከሆነ፡ ጴጥሮስ እና ሌሎች ሐዋርያትም የተሳሳተ ነገር አስተምረዋል ማለት ነዋ፥ ምክንያቱም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለ እያንዳንዱ ሰው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠምቋል።

አንድም ሰው “በአባት፡ በልጅ፡ በመንፈስ ቅዱስ ስም” አልተጠመቀም፡ ይህ የካቶሊክ ትምህርት ነው። በራሳቸው ቃላት፡ እና በራሳቸው መዝገበ ቃላት እና በሁሉም ነገር ላረጋግጥላችሁ እችላለሁ። የካቶሊክ እምነት እንጂ የ—የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት አይደለም። እና አንድም ሰው...

489 የኢንግላንድ ንጉስ እንኳን ሳይቀር የተጠመቀው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው። የመጨረሻው ሐዋርያ ከሞተ ከስድስት መቶ ዓመታት በኋላ፡ ያኔ መጠሪያዋ “ኤንጅል ላንድ” እንጂ፡ ኢንግላንድ ተብላ አትታወቅም ነበር። ስሙ የመጣውም፡ ከዚህ ነው። እርሱም በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቀ።

490 እንዲያምን ያደረገችው ነገር፡ ትንሽዬ ድንቢጥ ናት። ት... ትዝ ካለኝ፡ ሴንት አንጀሎ አይመስለኝም። አሁን፡ ስሙ ማን ነበር? አጋቦስ፡ ሴንት አጋቦስ፡ ይመስለኛል፡ አሁን፡ ስለ ስሙ እርግጠኛ አይደለሁም። ብቻ ግን፡ ለማንኛውም፡ ወደዚያ ወጣ፡ አንዳንድ ነገሮች ገጠማቸው...

491 ሕዝቡና አሦራውያንና ሌሎችም ጠቆር ያሉ ስለነበር፡ መልአክ ብለው ይጠሩአቸው ነበር፡ እና እነዚህ እንግሊዛውያን ረጅም፡ ነጭ፡ ጥቅልል ፀጉር፡ ባለ ወርቃማ-ጸጉር፡ እንግሎ-ሳክሰንስ፡ ታውቃላችሁ፡ ባለ ሰማያዊ-አይኖች ነበሩ። እነርሱም፡ “መላእክት ይመስላሉ” በማለት፡ “ኤንጅል ላንድ” ይሏቸው ነበር።

492 እና የ—የእግዚአብሔር አገልጋይ ወደዚያ ወጥቶ ለንጉሣቸው ሰበከ፡ እነርሱም በታላቅና፡ በተከፈተ ምድጃ ላይ ቆመው ነበር። በቅርብ ጊዜ ታሪኩን እያነበብኩት ነበር። አንዲት ትንሽ ወፍም በርሮ ወደ ብርሃን ገባና ተመልሶ ወጣ፡ ንጉሱም እንዲህ በማለት ጠየቀ፡ “ከየት መጣ እና ወዴትስ ሄደ? ” እያችሁ? “ወደ ብርሃን መጣ፡ እኛም አየነው፡ ወደ ጨለማም ተመለሰ። የሰው መንገድ ይህ አይደለምን? ” በማለት ተናገረ።

493 “ወደዚህ ከመምጣቱ በፊት ግን ምን ነበር? ” አለ ሰባኪው፡ እያችሁ። ይህም ንጉሡን ነካው፥ በማግስቱም፡ እርሱና ቤተሰቡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ። በትክክል።

494 ታዲያ ምን? በመረጨት የተጠመቀው የመጀመሪያው ሰው ማለት “በአባት፡ በልጅ፡ በመንፈስ ቅዱስ” ስም የተጠመቀው ሰው፡ በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ነው። ለመጀመሪያ ጊዜ መረጨት የተጀመረው፡ በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ነበር። የመጀመሪያው መድፋት የተጀመረው፡ በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ነበር። የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን ሁል ጊዜ የሚጠመቁት... በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ ሐዋርያት፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በማጥለቅ ነበር። በሁሉም ቦታ። ከዚህ ውጪ ያደረጉት አንድም ቦታ ፍልጋችሁ አሳዩኝ፡ እያችሁ።

495 አሁን፡ በዚህ፡ በዚህ ታላቅ ጊዜ፡ አይሁዶች በጭራሽ... እና ራባዩን ጠየቅኩት፡ እንዲህ በማለት፡ “መምህር ሆይ፡ ነብያትን ማመን ይከብድሃልን? ”

496 እርሱም “ነቢያትን እምናለሁ፡” አለኝ።

497 እኔም ጠየቅኩት፡ “በኢሳይያስ 9፡6 ላይ፡ ‘ወንድ ልጅ ተወልዶልናልና’ ሲል ምን ማለቱ ነው? የሚናገረው ስለ ማን ነበር? ”

498 እርሱም “ስለ መሲሑ እየተናገረ ነው፡” አለኝ።

499 “ታዲያ መሲሑ ይወለዳልን፡” አልኩት?

500 "አዎን፡ ይወለዳል።"

501 "እንግዲያውስ መወለድ ካለበት፡ እሱም... እናት ይኖረዋል፡" አልኩት።

502 "አዎን፡ እናት ሊኖረው ይገባል። አባትም፡ ሊኖረው ይገባል፡" በማለት መለሰልኝ።

503 እኔም; "በትክክል። ታዲያ ይህ ሊሆን የማይል ነገር ነው ብለህ እንድታምን ያደርግሃልን... ቀይ ባሕርን የከፈለ ታላቁ አምላክ እግዚአብሔር፡ በዚህ ሕፃን በንጽሕና መወለድ አይቻለውምን? " አያችሁ? ተያዘ።

504 እርሱም "ቢሆንም እርሱን ሦስት አማልክት ልታደርጉት አትችሉም፡" አለ።

505 "ሦስት አማልክት አይደለም፡" አልኩት። "መሲሑ ከእግዚአብሔር ጋር ምን ግንኙነት ይኖረዋል፡" አልኩት?

506 እርሱም "ራሱ እግዚአብሔር ይሆናል፡" አለኝ።

507 "አሁን ገባህ። አሁን ገባህ፡ እሱ አምላክ ነው፡" አልኩት። በትክክል ነው።

508 ከዚያም፡ "እንግዲህ፡ ይህ ሰው፡ የናዝሬቱ ኢየሱስ ሌባ ነበር። ሌባ ነበር፡" ሊለኝ ሞከረ።

509 እኔም ጠየቅኩት፡ "መምህር ሆይ፡ እንዴት ሌባ ነበር? "

510 "ይኸው፡" እንዲህ አለ፡ "መጽሐፍ ቅዱሳችሁ ራሱ እንዲህ ይላል 'በሰንበት ቀን ወደ እርሻ ገባና፡ እሸት ወሰደ።"

511 እኔም አልኩት፡ "እንግዲህ፡ ራባይ ሆይ፡ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ... ከዚህ የተሻለ እውቀት አለህ። የገዛ መጽሐፍ ቅዱሳችሁ ይህ ህጋዊ እንደሆነ ይመሰክራል፡ 'አንድ ሰው ከረጢቱን ሞልቶ መውሰድ አይችልም እንጂ፡ የፈለገውን ያህል እሸት ቀጥሮ መብላት ይችላል።' የራስህ ህግ፡ ራባይ።"

512 ወዲያውኑም ባለበት ቆም አለ፡ እና አ—አ—አምኗል፡ ምክንያቱም እ—እርሱም በቦታው ነበረ። እንዲህ አለ፡ በኋላ፡ እንዲህ አለ፡ "እሺ፡ በጆን አይን ላይ የተደረገው ም—ምንድነው... " "ምን አደረግክለት፡" ብሎ ጠየቀኝ?

513 "በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው፡" አልኩት።

514 "ኧህ።" አ—አያውቅም፥ "እንግዲህ፡ እግዚአብሔርን በሦስት ክፍሎች መቁረጥ አትችሉም፡" አለኝ።

515 እኔም አልኩት፡ "ራባይ ሆይ፡ እሱ በሥጋ የተገለጠው ያሕዌ ነበር። እ... የእርሱ ማንነት ያ ነበር፡ እርሱ ያሕዌ በሥጋ ነበር። የራሱ የሰዎች ሰሙ፡ የቤዛነት ስም እሱ ነበር፡ ከዚያ ከቤዛነት ሰዋዊው ስም በቀር ሰው የሚድንበት ስም፡ ከሰማይ በታች ሌላ አልተሰጠምና፥ እርሱም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በትክክል። እርሱ አምላክ ነበር፡ እርሱም አምላክ ነው፡ ለዘላለም አምላክ ይሆናል፡ ልክ ነው፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ።"

516 አሁን፡ የአህዛብ ቤተ ክርስቲያን በቅርቡ... የአህዛብ ቤተክርስቲያን አካል እንደምትጠናቀቅ አምናለሁ። በበሮች መካከል... ኢየሱስ፡ በማቴዎስ 24 ላይ፡ (ለአንድ ደቂቃ ያህል የመጽሐፍ ቅዱስ ቃሉን ልውሰድና)፡ እንዲህ አለ፡ "የአሕዛብ ዘመን እስኪፈጸም ድረስ የኢየሩሳሌምን ቅጥር ይረግጣሉ።"

517 አሁን ተመልከቱ። በማቴዎስ 24 ላይ፡ አይሁድ ከሥዕሉ እንደሚወገዱ፡ በጌታችን በኢየሱስ የተነገረ ነው። ዳንኤል፡ በቀደሙት ነቢያት፡ ለአይሁድ ሰባ ሱባዔ እንደሚጣልባቸው፡ ተናግሮአል። መሲሑም (አለቃው) መጥቶ በሰባኛው ሱባዔ መካከል ትንቢት እንደሚናገር፡ እነርሱም ሰባቱ ዓመታት ናቸው፡ በመካከልም እንደሚቆረጥ ተናገረ። ምን ያህል ፍጹም እንደነበረ ተመልከቱ፡ ኢየሱስ በትክክል ሦስት-ዓመት ተኩል ሰብኮ ተሰቀለ። ይሁን እንጂ ወደፊት ሦስት... እዚህ ጋር ሌላኛው ጥያቄ ላይ በትክክል መጥቷል። በእነሱ ላይ በአይሁዶች ላይ የቀረላቸው፡ ሦስት-ዓመት-ከ-ተኩል አለ። መሆንም አለበት።

518 አሁን ራዕይ 7 ኛ ምዕራፍ፡ ብትወስዱ፡ ዮሐንስ ከአሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገድ ከአይሁድ የታተሙትን፡ መቶ አርባ አራት ሺህ አየ። ምን ለማለት እንደፈለግኩ አያችሁ? ይህ ወደ ፊት የሚመጣው ነገር፡ አስቀድሞ ሊሆን የተገባ ነበር።

519 አሁን ከመዝጋታችን በፊት፡ ምን ያህል ቆንጆ እንደሆነ ተመልከቱ። እንዴት እንደሆነ—እንዴት እንደሚሰራ እዩት። አሁን፡ አይሁዶች ታውረው ቆይተዋል።

520 አሁን፡ እነዚህ አይሁዶች፡ አብዛኞቹ እዚህ ያሉት፡ እነዚህ... እንዴት እንደሆኑ ታውቃላችሁ፡ የዓለምን ሀብት ይዘዉታል። ብቻ የገንዘብ—ሰዎች ናቸው፡ እነርሱ ጋር ማየት የምትችሉት ያ ብቻ ነው፡ አያችሁ፥ እጅግ አብሪተኞች፡ እና ግዴለሽ ናቸው፡ አይሰሙም። ነገር ግን፡ በደንብ ካስተዋላችሁ፡ እሱ የሚናገረው ስለ እነሱ አይደለም።

521 አሁን፡ አሕዛብ... አሁን ተከታተሉኝ፡ ለእነዚህ አይሁዶች ገና ሦስት-ዓመት-ከ-ተኩል ይቀራቸዋል። አሁን፡ ኢየሱስ እንዳለው የአሕዛብ ሙላት እስኪገባ ድረስ ኢየሩሳሌም ከተማ በአሕዛብ ትረገጣለች ብሏል... (እንግዲህ፡ በዘመን ሙላት የማታምኑ ሰዎች፡ ይሄስ ምን ትሉታላችሁ? )... የአህዛብ ዘመን እስኪገባ ድረስ። የአሕዛብም ሙላት ሲገባ (የአሕዛብ ጊዜ በተፈጸመ ጊዜ)፡ ከዚያም ከተማይቱ ለአይሁድ ትሰጣለች። ኢየሱስም ስለ ትውልዱን ተናገረ... አለም፡ "በለሲቱ ስታቆጠቁት ስታዩ፡ ሌሎች ዛፎችም በሙሉ ሲያቆጠቁጡ፡" "ክረምት እንደቀረበ ታውቃላችሁ፡" ብሏል። አለም፡ "እንዲሁም እነዚህ ነገሮች ሲፈጸሙ ስታዩ፡ ዘመኑ ቀርቦ፡ በደጅ እንደ ሆነ እወቁ፥ እና እውነት እላችኋለሁ እነዚህ ነገሮች እስኪፈጸሙ ድረስ ይህ ትውልድ አያልፍም።"

522 አሁን፡ "እሱ የተናገረው ለዚያ ነው በማለት፡" ያን ጊዜ የነበረው ትውልድ ያንን ጠበቁት። በፍጹም አይደለም!

523 አዳምጡ! እርሱ ያለው፡ "የበለስ ዛፍ ስታቆጠቁጥ ያሚያይ ትውልድ።" አሁን ተመልከቱ፡ "የበለስ ዛፍ፡ እና ሌሎች ዛፎች፡" አለ። አሁን፡ በሌላ አባባል፡ "በዚያን ዘመን ሁለንተናዊ ሪቫይቫል ይኖራል።" አሁን ይህን ትንቢት፡ እንዴት እንደሚሰራ እና ልክ ፍጹም በሆነ መልኩ እንደሚዋሃድ ተመልከቱ። አሁን ተመልከቱ። "ሌሎች ዛፎች ሲያቆጠቁጡ፡ ሪቫይቫል።" ዛፍ፡ ስታቆጠቁጥ ማለት ትርጉሙ፡ ሪቫይቫል ነው። ልክ ነው? አሁን፡ የትንቢት አስተማሪ፡ የሆነ ሰው ሁሉ፡ የበለስ ዛፍ ማለት ሁሌም አይሁድን እንደሆነ ያውቃል። ያንን እናውቃለን። አይሁዳውያንን ነው። አሁን...

524 ኢዩኤል ላይ ተመልከቱ፡ እሱ ሲናገር፡ እንዲህ አለ፡ “ከተምች የተረፈ፡ ኩብኩባ በላው፡ ከኩብኩባ የተረፈ፡ አንበጣ በላው፡ አንበጣ የበላው... ” ካስተዋላችሁ፡ ይህ ትል ተመሳሳይ ትል ሆኖ፡ በተለያየ ዑደት ነው፥ ተምቹ፡ ኩብኩባው፡ አንበጣው ያው ነው። ሁሉም አንድ አይነት ነፍሳት ነው፡ የህይወቱ የተለያየ ዑደት ላይ መሆኑ ብቻ ነው። አሁን ተመልከቱ፡ ያው ትል ያንን የአይሁድ ዛፍ በልቶ፡ ጣለውና፡ ከዚያ በኋላ መብላቱን ቀጠለ አሁንም ጉቶ እስኪሆን ድረስ በላ በላ እና በላ፥ በኋላ ግን እንዲህ አለ፡ “‘እመልሳለሁ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፥ ‘ኩብኩባ የበላባቸው ዓመታት ሁሉ። ሕዝቤንም ለደስታ አደርገዋለሁ።” አያችሁ? አሁን፡ ዛፉ ተበልቷል። አህዛብ በእሱ ውስጥ ገብተዋል፡ እውነት ነው። ስለዚህ፡ ፍሬ ማፍራት አለብን።

525 አሁን የመጨረሻው ጊዜ ሲመጣ፡ ከተረዳሁትወደ መጨረሻው ስንደርስ (በትክክል ካየሁት)፡ በወንጌሉ፡ ታላቅ ሪቫይቫል ይኖራል ተብሎ ይጠበቃል።

526 አሁን፡ የአይሁዶች ባንዲራ በዓለም ካሉት ባንዲራዎች ሁሉ እጅግ ጥንታዊው መሆኑን ታውቃላችሁ? እናም ላለፉት ሁለት ሺህ አመታት እንደውም ከዚያ በላይ፡ ላለፉት ሁለት ሺ-አምስት መቶ አመታት፡ ከጥቅም ውጪ ሆኖ ቆይቷል። የአይሁዶች ባንዲራ፡ ያ ባለ-ስድስት ጠርዝ የዳዊት ኮከብ፡ ለሁለት ሺ-አምስት መቶ ዓመታት ተውለብልቦ አያውቅም፥ ይህም ወደ ባቢሎን—ከተወሰዱ ጊዜ ጀምሮ ነው። እንዲሁም፡ የሮማ አገዛዝ ስለያዛቸው (መሲሕ መጥቶ ስለካዱትም)፡ ወደ አራቱም የምድር ነፋሳት ተበተኑ። ግንቦት ስድስት ቀን፡ 1946 ግን፡ ባንዲራዋ በኢየሩሳሌም እንደገና መውለብለቧን፡ ታስታውሳላችሁን? (በማግስቱ) በግንቦት ሰባት፡ 1946 ላይ፡ የጌታ መልአክ እዚህ እንደተገለጠልኝ፡ እና ወደ ምድር ሁሉ፡ ሪቫይቫል አመጣ ዘንድ እንደላከኝ ታውቃላችሁን? በማግስቱ ጠዋት! ያ ባንዲራ በእየሩሳሌም ሲውለበለብ፡ በዚያን ቀን ከሰአት በኋላ ፀሐይ ስትጠልቅ፡ የጌታ መልአክ በተመሳሳይ ጊዜ እዚህ ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ታየ። “በለሲቷ እና የቀሩት ዛፎች ሲያቆጠቁጡ ስታዩ!”

527 እዚህ በኦሃዮ ወንዝ ዳር የታየውን ኮከብ ሰንቶች ታስታውሳላችሁ፡ ከብዙ አመታት በፊት፡ ሲናገር... እሱ ሲወርድ እስካሁን ድረስ፡ የእሱ ምስል እዚህ አለ። እንዲህ አለ፡ “ዮሐንስ የመጀመሪያውን መምጣት ለማብሰር እንደመጣ፡ መልእክትህም የዳግም ምጽአት ለማብሰር ይወጣል።” አሁንም፡ ተመልከቱ፡ በምድር ሁሉ ላይ ሪቫይቫል ተቀጣጥሏል። በአሰር ሺዎች ጊዜ ሺዎች እና ሺዎች፡ ታላቅ የሆነ ሪቫይቫል ነው።

528 ሁሉም ወገጥባቂዎች፡ እና በሀገሪቱ ዙሪያ ያሉ የተለያዩ ሰዎች፡ እና ትልልቅ አብያተ ክርስቲያናት እንዲህ አሉ፡ “የቢሊ እሁድ ቀናት አብቅተዋል” ይሉኝ ነበር። ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን ሪቫይቫል ስትጀምር ባዩ ጊዜ (በተራው ሕዝብ)፡ ፊታቸውን መሰወር ጀመሩ። ቻርለስ ፉለር በቦታው መሆን ይችል ነበር፡ ነገር ግን በጣም አርጅቶ ስለነበር፥ ስለዚህ ከቢሊ ግራሃም ጋር ሆኑ። እግዚአብሔርም ቢሊ ግራሃምን ተጠቀመበት፡ ወይም፡ የባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን ተጠቀመችበት፡ ሁሉም በዙርያው ተሰበሰቡ። እና ሰባኪ ከተባለ፡ ቢሊ ግራሃም የወንድም ኔቪል ግማሽ ያህል የመሰበክ አቅም የለውም፡ በጭራሽ... በ፡ በጭራሽ። ግን ምንድን ነው? ይህ ይፈጽሙት ዘንድ ስለተገባቸው፡ አካላቸው ስለሆነ፡ ሁሉም ሰው፡ በዙሪያው ተሰበሰበ። ቢሊም

ተመሳሳይ ነገር ተናግሯል። እያችሁ፡ መፈጸም ነበረባቸው። የእግዚአብሔርንም ቃል መፈጸም መደረግ ነበረበትና። በዙሪያው የሚሰበሰቡበት መንፈስ ስላልነበራቸው፡ በዙሪያው ለመሰባሰብ ቃሉን መጠቀም ነበረባቸው፥ እንዲሁም አደረጉ። እና ቢሊ የቃል ሰባኪ ነው፡ ቆፍጣናም ነው፡ በዙሪያውም ተሰበሰቡ፥ ይህም ተራዎቹ ሁሉ በእንቅስቃሴዎቻቸው ላይ እንዲገኙላቸው በማሰብ ነው። እና መለኮታዊ የሆነው ነገር፡ መለኮታዊ ፈውስ፡ እና በእግዚአብሔር ተአምራት የሆኑ፡ ስልጣኖች እና ሥራዎች ወዘተ፡ ይህች ያዘች... ቤተ ክርስቲያኒቱ፡ በመቅረዟ ውስጥ ዘይት የያዘችውን ሙሽራ፡ ሪቫይቫል ውስጥ ገባች። እያችሁ? ተራዋ እና ቀዝቃዛዋ ቤተ ክርስቲያን የራሷ ሪቫይቫል አዘጋጀች። እነሆ እስራኤልም የራሳቸውን ሪቫይቫል እያደረጉ ነው።

529 አሁን በቤቴ **ሰሪ ሚኒትስ ቲል ሚድናይት** የተባለ፡ ፊልም አለኝ። እነዚያም አይሁድ ሲገቡ የሚያሳይ ምሥል ይታያል። **ሉክ** መጽሔት፡ ሲገቡ ያሳያል። መርከቦቹም፡ ተጭነው፡ ከኢራን ወደ ታች ወርደው በዚያ ይጓዛሉ፥ ኢየሱስ በምድር ላይ እንዳለ አይሁዶች በጭራሽ አላወቁም ነበር፡ በባቢሎን ምርኮ ወደዚያ ወረዱ። መቼም የሚያውቁት ያ ብቻ ነው። እረሱ... **ሉክ** መጽሔት ላይ፡ **በላይፍ** ወይም ሌሎች ላይ ባረጁ የእንጨት እቃዎች ሲያርሱ ይታያሉ። እናም እነዚያን አውሮፕላኖች ሲገቡ ባዩ ጊዜ፡ "ይህ ነው፡" ብለው አሰቡ፡ እግዚአብሔርም "'እነሱ ወደዚያ እንደሚመለሱ፡ ወደ ኢየሩሳሌምም በንስር ክንፍ እንደሚመልሳቸው' ነገራቸው።" ትክክል። በእዚያም አሉ። አይሁዳውያንም "ይህ ነው፡" አሉ። ሰፍራውንም ረገጡ፡ እኛም ቃለ መጠይቅ የተደረጉበት፡ ፎቶዎቻቸው እና ድምጻቸው ይዘናል፥ ከመላው ዓለም የመጡ። አንዳንዶቹ አሮጌዎቻቸውን በጀርባቸው ላይ አዝለው፡ ዓይነ ስውር እና አካል ጉዳተኞችም እንዲሁ። እና ከተለያዩ የአለም ክፍሎች ከመርከቦቹ እየወረዱ፡ ወደ ውስጥ ገቡ።

530 እና በማዳበሪያዎች ውስጥ፡ ድንጋዮችን ከመሬት ላይ መልቀም ጀመሩ፥ እና ዛሬ የውሃ ምንጮችን አገኙ፡ ይህም በዓለም ላይ፡ እጅግ በጣም ትልቁ የግብርና አገር ሆናለች። ሙት ባህር ከሌላው ዓለም ሁሉ የበለጠ ሀብትን አምቋል። አይሁዶች እየተመለሱ ናቸው፥ ከአሕዛብ ዘንድ ተሰውሯል፡ ቢሆንም እንደ ጽጌረዳ እየፈኩ ናቸው።

531 እነዚያን አይሁዶችን—እንዲህ አሏቸው፡ "በገዛ አገራችሁ ልትሞቱ እየመጣችሁ ነው፡" አሏቸው።

532 "መሲሑን ለማየት እየተመለስን ነው። እሱ የት ነው ያለው? እሱ እዚህ መሆን አለበት፡" ይሉ ነበር።

533 ወንድሜ ሆይ፡ በለሲቷ ጫፏ ሲያቆጠቁጥ ስታዩ፡ እንዲህም አለ፡ "ይህ ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ ይህ ትውልድ አያልፍም።" የተራዋ ሪቫይቫል ተመልከቱት። የቤተ ክርስቲያን ሪቫይቫልን ተመልከቱት። በአይሁዶች የመጣውን ሪቫይቫል ተመልከቱት፡ እነሱ የመሲሑን መምጣት እየተጠባበቁ ነው። ቤተክርስቲያን፡ በመንፈስ-የተሞላች ቤተክርስቲያን፡ ሙሽራዋ መ... በመብራታቸው ዘይት የያዙ ደናግል ወደ ሰርግ እራት ይሄዳሉ።

534 አይሁድም እንዲህ ይላሉ፡ "ይኸው የጠበቅነው አምላካችን። ይህ ነው።" አንድ መቶ አርባ-አራት ሺዎቻችሁ ማለት እነዚህ ናቸው... ሩስላይቶች

ተቀላቅለውባቸዋል። እሱን የሚቀበሉት በዚያ ቆመው ያሉ አይሁዶች አሉ። "ይኸው የጠበቅነው አምላካችን ይህ ነው፡" ይላሉ። እርሱንምያዩታል፡ ይሉታልም፡ "በእጅህ ላይ ያሉትን ጠባሳ ከየት አገኘሃቸው? በምን ምክንያት መጡብህ? "

535 እርሱም ይላቸዋል፡ "ከወዳጆቼ ቤት አገኘኋቸው።" ልክ ነው፡ "ከወዳጆቼ ቤት ነው።"

536 ምን ያደርጋል? የአሕዛብ ቤተክርስቲያን ወደ ክብር ትወሰዳለች ሙሽራይቱም ከክርስቶስ ጋር ትጋባለች።

537 ዮሴፍ ራሱን ለሕዝቡ ያሳወቀው እንዴት ነው? አሕዛብን ሁሉ ከፊቱ ካሰናበተ በኋላ ነው። በእርግጥ ያደረገው እንዲሁ ነው። የሴቲቱ ዘር ቅሪት ምን ይሆናል? ዘንዶውም ሊዋጋ ከአፉ ውኃ ያወጣል፥ ኢየሱስም፡ "በውጭም ወዳለው ጨለማ ውስጥ ይጣላሉ፡ በዚያም ልቅሶና ዋይታ ጥርስ ማፋጨት ይሆናል፡" ታላቁ የሰደት እና የፈተና ሰዓታት ወደ አህዛብ ቤተ ክርስቲያን ይመጣል።

538 ነገሩ እንዴት ሊሆን ነው? ያኔ ሰማዕትነት በተጀመረ ጊዜ፡ እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ከአይሁዶች ከለየ በኋላ፡ ኢየሱስ እንደ ዮሴፍ ተመልሶ ይመጣል። ዮሴፍን በሰሙ ጊዜ፡ ጠባቂዎቹንና ሌሎችን ሁሉ ባሰናበተ ጊዜ፡ እናም ታናሹን ብንያምን እና ሌሎቹ ቆመው አያቸው፡ እነሱም ዮሴፍን ስለ ገደሉ ንስሃ ሲገቡ ታዩ። እነሱ ዮሴፍን የገደሉት መሰሏቸው ነበር፡ እሱ ግን በፊታቸው ቆሞ ነበር። እንዲህም አላቸው፡ "እኔ ዮሴፍ ነኝ። እኔ ወንድማችሁ ነኝ።"

539 ከዚያም በእውነት ተንቀጠቀጡ፡ "እሱ ዮሴፍ ነው። አሁን አውቀነዋል አሉ።"

540 እርሱ ደግሞ "እኔ ኢየሱስ ነኝ። እኔ መሲሁ ነኝ፡" ይላቸዋልና።

541 "ኦህ፡ ማይ፡ አሁን ምን እንቀበላለን!" ይላሉ፡

542 ሁሉም የተደረገው ስለ እግዚአብሔር ክብር ነው። አይሆንም... እንግዲህ፡ ዮሴፍ፡ በፈርዖን ቤተ መንግሥት ሲያለቅስላቸው ሰምተውት ነበር።

543 ኢየሱስ እኛ አሕዛብ የመግባት እድል እንዲኖረን እርሱ በዕውርነት የመታቸው እነዚያን አይሁዶች እስኪያይ ድረስ ጠብቁ፡ እላችኋለሁ፡ ልዩ ጊዜ ይሆናል። እነዚያን አይሁዶች ይወስዳቸዋል፡ በፍጹም አትጨነቁ፡ እነርሱ አይሁዶች ይድናሉ። አዎን፡ ወዳጄ፡ ወደዚያ መምጣቱ የማይቀር ነው። ይህም የእኔ ሀሳብ ነው፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የትም ማየት አልችልም። እንደገናም፡ ሦስቱን አንድ ላይ መረዳት አለባችሁ።

544 እንቅልፋሟ ድንግል—መረዳት አለባችሁ፡ ተራዋ ቤ—ቤተ ክርስቲያን፡ ተናዛዥዋ፡ እያችሁ። ቤተ ክርስቲያኒቱ ተረዷት... በመጀመሪያ አይሁዳዊው ነው፡ እንደታወረ ሰው፡ ዳር ሆኖ የሚጠባበቅ፡ መጀመሪያ አይሁዳዊ። እንደቀጣይ እርምጃ መውሰድ ያለባችሁ፡ ሰነፏ ድንግልን ነው፡ ፈዛዛ ስለሆነኑ፡ ወደ ቸርችነት ተቀየሩ፡ ቸርች አባል ሆኑ፡ እና በጣም ተከታይ ናት። ከዚያ በመቀጠል፡ የምትነጠቀዋ፡ መንፈሳዊቷን ቤተክርስቲያን መረዳት አለባችሁ፡ ሙሽራይቱን፡ ቆማለች። እነዚህ ሶስት አካላት፡ አይቀላቀሉም... በጭራሽ፡ አንድ አይሆኑም። ሁሉም አንድ አይደሉም። የይሖዋ ምሥክር እንደሚሉት አይደለም፡ "መቶ አርባ-

አራት ሺዎቹ የሙሽራይቱ አካል ናቸው” ይላሉ፥ ስህተት ነው። እነሱ አይሁዶች ናቸው፡ አያችሁ። ሙሽራዋ፡ አይሁዶች፡ እና ስነፏ ድንግል ናቸው። እናንተም አይታችሁ፡ “እንግዲህ፡ እነዚህ በሦስት የተለያዩ ሰፍራ ያሉ ናቸው፡” ትላላችሁ። ሁሉም፡ ሶስት የተለያዩ የሰዎች ምድቦች ናቸው። በእርግጥ፡ አንድ አይሆኑም።

545 ከዚያ በኋላ ኢየሱስ ወደ ምድር ሲመለስ... አይሁዶቹ፡ ማን ይሆናሉ? የቤተ መቅደሱ ጃንደረቦች ይሆናሉ። ኢየሱስም ሲመለስ፡ ከሙሽሪት **ጋር** ይመጣል። ኢየሱስ ሦስት ጊዜ ይመጣል፥ ለመጀመሪያ ጊዜ ቤተክርስቲያኑን **ለመቤዠት** መጥቷል፡ ለሁለተኛ ጊዜ ቤተክርስቲያኑን **ለመውሰድ** ይመጣል፡ ለሦስተኛ ጊዜ ከቤተክርስቲያኑ **ጋር** ይመጣል። ተመልከት? በትክክል። ስለዚህ ሁሉም አንድ ታላቅ ፍጹም መምጣት ነው፡ እርሱም አንድ ታላቅ ፍጹም አምላክ ነው፥ ይህ ሁሉ አንድ ታላቅ ፍጹም ክርስቶስ ነው፥ አንዲት ታላቅ ፍጹም ቤተክርስቲያን፡ ታላቅ ፍጹም ቤዛነት፡... ሁሉም ነገር፥ በሥላሴአዊ መልኩ ይመጣል፡ ሁሉም ግን በአንድ ነው። አያችሁ? **ይህ** ሦስት ሰዎች ማለት አይደለም፡ ሦስት አይደለም፥ አንድ ሰው፡ አንድ ቤተ ክርስቲያን፡ አንድ አካል፡ አንድ ክርስቶስ፡ አንድ ጌታ “በሁላችሁም፡ በሁላችሁም በኩል፡” እና የመሳሰሉት። ሁሉም አንድ!

546 ጌታ ይባርካችሁ። በጣም አቆይቻችኋለሁ።

547 ጌታ ፈቃደኛ ሆኖ፡ አሁን፡ በጥቂት ምሽቶች ውስጥ፡ ወይም እሁድ ምሽት ወይም እንደዚያ ነገር እንደገና ብመጣ፡ ፓስተር በልቡ ላይ የሆነ ነገር ከሌለ፡ ለእነዚህ ደግሞ መልስ ለመስጠት እሞክራለሁ። ኦህ፡ ሌሎች ቆፍጣናዎችም አሉ። ሰንቶቻችሁ ከእነሱ መሰማት ትፈልጋላችሁ? ኦህ፡ እጅግ እወዳቸዋለሁ። አገልግሎቱን ወደ መጋቢ ከመስጠታችን በፊት፡ እንደገና፡ በፍጥነት ልጥቀሳቸው።

548 ይህንን አዳምጡ፥

> **ድንጋዮቹ በ-... ? እነዚህ በራእይ 21 ላይ፡ የሚገኙ ድንጋዮች ምን ያመለክታሉ?** ጥሩ ነው።
>
> **በራዕይ 5 ላይ ያሉትን አራቱን አራዊት አብራራ።** ይሄም ሌላ ጥሩ ነው።
>
> **ሃያ-አራቱ ሽማግሌዎች እነማን ናቸው?** እዚህ ጋርም ሌላ ጥሩ ነገር ነው፡ አያችሁ።
>
> **በዘፍጥረት 38 ላይ ያለው ቀይ ክር ምን ማለት ነው?** ሄዶ-ምራቱን-ወሰዶ ከእርሰዋ ጋር እንደ ጋለሞታ ሲተኛ፡ ታስታውሳላችሁ፥ እና ዋጋውን ተናገግሮ ጨረሰ፥ ከዚያ በኋላ ልጁ ሲወለድ፡ ቀዩን ክር በእጁ ላይ አደረጉበት (ገፋቶ ወጣ ከዚያም ተመልሶ ገባ)፡ የ—የሚቀጥለው ቀድሞት ወጣ። ኦህ፡ ይህ ጥሩ ነው፡ በእውነትም ነው።
>
> **በራእይ 11 ላይ፡ የምስክሮችን ሞት በተመለከተ የሚላኩት ስጦታዎች ምንድን ናቸው?** ሙሴ እና ኤልያስ ለሪቫይቫል ወደ እነዚህ መቶ-አርባ አራት ሺህ የሚመለሱት ያኔ ነው። **ስጦታዎቹ ምንድን ናቸው?** ምን እንደሆኑ ተመልከቱ፡ ይህ ቆፍጠን ያለ ነገር ነው።

**ከአንድ ሺህ-ዓመታት በኋላ ቅዱሳን የት ይሆናሉ...** (ይሄኛውም በጣም ጥሩ ነው፡ ወዳጄ። እ... )**... ይነግሣሉን? ምን ዓይነት አካል ይኖራቸዋል?**

**በመላእክት እንዴት እንፈርዳለን?**

**በአንደኛ ቆሮንቶስ ፀጉር ለምን የመላዕክት ሆነ? በአንደኛ ቆሮንቶስ መጽሐፍ።** አንዳንድ ጥሩ፡ በጣም ጥሩ ናቸው።

549 ጌታ ይባርካችሁ። አንድ እንድንሰባሰብ እና እነዚህን ነገሮች እንድንወያይ ጌታ እንደፈቀደልን ተስፋ አደርጋለሁ፡ ሁሉም ለክብሩ ነው። በሃሳቦች ላይ ላንስማማ እንችላለን፡ ግን አንድ ነገር እላለሁ፡ እኔ ስለ እነርሱ እንደማወራው ሁላችሁም እነርሱን ስትሰሙ ብዙ ደስታ ካገኛችሁ፡ አስደሳች ጊዜ እያሳለፍን ነው። ኣሜን። ኣሜን።

550 እሺ፡ ጌታ አሁን ለሁላችሁ መልካም ይሁን። አገልግሎቶቹን አትርሱ። የወንድም ኔቪል ስርጭት፡ አሁን፡ በWLRP፡ ቅዳሜ ጥዋት በዘጠኝ ሰአት ይተላለፋል፥ የኔቪል ኳርትት፣ እንደሚባርኳችሁ እርግጠኛ ነኝ፡ ከፍታችሁ ስሙት። እና ከቻልኩ፡ በጊዜ ብመለስ፡ ወይም እንደምመለስ ካየሁ፡ ሚስቴን እጠራታለሁ፥ ውድ ወንድሜ ቦስዎርዝን ለማየት ጌታ ከፈቀደልኝ። እ... ሁላችሁም... እሁድ ምሽት እመለሳለሁ።

551 ጌታ አሁን መልካም ይሁንላችሁ። ወንድሜ፡ ፓስተር፡ አንድ ደቂቃ ወደዚህ ና፥ አገልግሎቱንም ይውሰድ። እና፥

> የቤተሰብ ጸሎት አትርሱ፡
> ኢየሱስን በዚያ ልበሱ፡
> ሸክማችሁን ይወስደዋል እሱ፡
> እነሆ፡ የቤተሰብ ጸሎት አትርሱ።

552 ወደዳችሁት? ስንቶቻችሁ በቤታችሁ ትጸልያላችሁ? እስኪ እንየው፡ ሁ... ሁላችሁ... በጣም ጥሩ፡ ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ። መልካም ሁኑ፡ ልጆች፡ እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

እሺ፡ ወንድም ኔቪል።

57-1002 ጥያቄ እና መልስ በዕብራውያን ክፍል II
ብራንሃም ተበርናክል
ጀፈርሰንቪል, ኢንዲያና ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2024 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org